# *ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ ቤን EthiopiaFirst እና “The New Face of Ethiopia” ዶኩሜንታሪ ፤*

**(በእናኑ አጎናፍርና ጓደኞቿ enanu_agonafer@yahoo.com)**

***መግቢያ***

በቅርቡ Youtube አይታችሁ ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከ EthiopiaFirst ድረ ገጽ ባለቤት ጋር November 26, 2009 ያደረጉት ቃለ መጠይቅ በአራት ክፍል ቀርቦ ታገኛላችሁ። በ EthiopiaFirst ድረ ገጽ ላይም አለ። ብዙዎቻችሁ እንዳላያችሁት እንገምታለን። ትዕግስት ካላችሁ ብታዩት አይከፋም። ጠያቂው ጠቅላይ ሚኒስትሩን ከማግኘቱ በፊት ቃለ መጠይቁን የሚያደርገው በኢትዮጵያ ቆይታው ለሚሰራው ዶኩሜንታሪ እንዲረዳው እንደሆነ ይናገራል። ገና ከመጀመሪያው በጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃ ስልሆነ ይመስለኛል “መደናገጥ ይታይብኛል” በማለት ተደናግጦ ሊያደናግጠን ይሞክራል። አፍታም ሳይቆይ “ I really want to talk to him - ፊት ለፊት - አለ አይደለ?” በማለት ደፍሮ ሊያደፋፍረን ይሞክራል። መልሶ ደግሞ “I am scared” ይላል። የጠያቂው የተደበላለቀ ስሜት ቀልባችንን ለመሳብ የከወነው ቲያትር መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሲያገኝ ከሚያሳየው ሁኔታ እንረዳለን። አንዳችም የመደናገጥም ሆነ የመፍራት ፍንጭ አይታይበትም። የፈገግታው፣ የሰላምታው ጋጋታና የመቀመጫ አመራረጡ ቤተኛ እንጂ እንግዳ አያስመስለውም። ቃለ መጠይቁ እየገፋ ሲሄድ እንዲያውም የጓዳዊነት ስሜት እያንጸባረቀ ይሄዳል።

ጠያቂው “ቤን ከ EthiopiaFirst” በማለት ራሱን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስተዋውቃል። አስከትሎም እርሳቸውን ያመስግንና ከውጭ ሃገር እንደመጣ፣ የምንም ፓርቲ አባል እንዳልሆነ፣ ጥሩ ነገር ሲያይ ደስ እንደሚለው፣ ድክመቶችን ሲያይ boldly እንደሚናገር ይነግራቸዋል። ዳር ዳር የሚለው ገለልተኛ ነኝ ለማለት ነው። “ቤን EthiopiaFirst” ስሙ ይሁን አይሁን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አልጠየቁትም። ስለ ስሙ የተጨነቁም አይመስሉም። ምናልባት በረዳቶቻቸው የፈላደልፈያው ብንያም ከበደ መሆኑ ተነግሯቸው ይሆናል። ዝም ብለው በፈገግታ ያዳምጡታል። እዚህ አገር የምንኖር ሰዎች ጠቅላይ ሚኒስተሩን ብንፈራ ምክንያት አለን። ምክንያቱ ግልጽ ስልሆነ ለማንም ማስረዳት ይገባናል የሚል ግምት የለንም። የቤን ድርጊት ቲያትር ቢሆንም ከውጭ ሃገር በተለይም ነጻነት ካለበት አሜሪካን የመሰለ ሃገር የመጣ ሰው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ቃለ መጠይቅ ላደርግ ስለሆነ ተደናግጫልሁ፣ scared ሆኛለህ ማለቱ  እዚህ ሃገር የምንኖር ሰዎች የምንገፋውን የመከራ ኑሮ ሳያስበው ማንጸባረቁ ነው። ምናልባትም የዚያ ዓይነት የፍራቻ ቲያትር ባይሰራ ኖሮ ሰውየውን ማነጋገር ባልቻለም ነበር። ዘዴው በሚገባ ሰርቷል።

ብዙዎቻችን ***ቤንን***  የምናውቀው EthiopiaFirst ድረ ገጽ ላይ በሚጽፈውና በሚናገረው ነው። እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ EthiopiaFirst ድረ ገጽ የቻይና ኢንተርኔት ማፈኛ ቴክኖሎጂ የማይነካው እኛም ያለአንዳች ፍራቻና ችግር ከፍተን፣ መልከት መልከት አድርገን የምንዘጋው ድረ ገጽ ነው። ***ቤን*** የገዢው ፓርቲ አባል ባይሆንም ደጋፊ መሆኑን እንገምታለን። በዚህም ቃለ መጠይቅ ወቅት እንኳ ወገናዊነቱን ለማሳየትና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ላለማስቆጣት በማሰብ ሳያነሳ ያለፋቸው በርካታ መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ በሃገሪቱ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች መጣስ ሁኔታ፣ የተቃዎሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ያላባራ ወከባ፣ የነጻ ጋዜጠኞች በእስርና በስደት መንገላታት፣ የሃይማኖቶችና የብሄር ብሄረሰቦች ግጭቶች፣ ለሱዳን ሊሰጥ ሽር ጉድ የሚባልለት ሰፊ መሬት፣  ሃገሪቱን ያሽመደመደው ሙስና (corruption)፣ የገዢው ፓርቲና

የሸሪኮቹ የንግድ ድርጅቶች (endowment companies) የመሰረቱት oligarchy የግሉን ንግድ ማዳከም እንዲሁም ህዝቡን በሆነው ባልሆነው ማስጨነቅ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ***ቤን*** ድንቄም ገለልተኛ የሚባል ዓይነት ነው።

***ቤን*** የገዢው ፓርቲ ደጋፊ ሆነም አልሆንም በቃለ መጠይቁ ወቅት አንድ መካድ የማይቻል እውነታ አሳይቷል። ከዚህ በፊት በጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ ያልተሰጠባቸው አዳዲስ ጥያቄዎች ባያነሳም እያዝናና ሲቻለውም እያዘናጋ እጅግ መሰረታዊ ጥያቄዎችን አቅርቦላቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ ፌደራሊዝምና የሃገሪቱ አንድነት ጉዳይ፣ የረሃብና የምግብ እጥረት ችግር፣ ለውጭ ኢንቬስትሮች በመሰጠት ላይ ያለው የእርሻ መሬት፣ መጪው ምርጫና ዳያስፖራው ይገኙበታል። እርሳቸው የሰጧቸውም መልሶች ቢሆኑ ቀደም ብሎ ለተመሳሳይ ጥያቄዎች ከሰጧቸው መልሶች ብዙ ባይርቁም በማብራሪያቸውና በአጽንኦታቸው ከወትሮው ይለያሉ። የሃገራችን አንድነት አስተማማኝ ነው፣ የምግብ እጥረት እንጂ ረሃብ የለም፣ በኪራይ የተሰጠው መሬት ጥቅም ላይ ያልዋለ ነው፣ በመጪው ምርጫ የ 1997 ቱ ሁኔታ አይደገምም፣ የዳያስፖራው የአመጽ ድርጊት ነውር ነው ይላሉ። የተቀሩት ጥያቄዎች  ስለግል ህይወታቸው ሆነው፣  ሥራ ሲለቁ የት እንደሚኖሩና ምን እንደሚሰሩ የሰጧተውን መልሶች ይዟል።

እንግዲህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሃያ ዓመታት በላይ ስልጣን ላይ መቆየታቸው አልቀረም። ከአሁን በኋላ በስልጣን ላይ የሚቆዩባቸው አምስት፣ አስር ወይም ሃያ ዓመታት ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት በስልጣን ከቆዩበት በፈጠን ሁኔታ ወደ ተሻለ ህይወት ወይም የባሰ ውድቀት ያመራናል የሚል ግምት አለ። ይህ ግምት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አለው ማለት አይደለም። አንዳንዶች የሰውየው ስልጣን ላይ መቆየት የፈጠነ ውድቀት እንጂ የተሻለ ነገር አያመጣም ሲሉ ሌሎች ደግሞ ተቃራኒውን ይናገራሉ። እኛ ሁለቱም ሊሆኑ ይችላሉ ባይ ነን። ነገር ግን ከሁለቱ የየትኛው ሚዛን በምን ምክንያት እንደሚደፋ ለመገመት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰውየው የሚሉትን ሁሉ በጥንቃቄ ማዳመጥና ማሰላሰል ከተቻለም መመርመር ያስፈልጋል።

በዚህ አጭር ጽሁፍ ማድረግ የምንሞክረው ሁለት ነገሮችን ነው። አንደኛው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለ***ቤን*** ጥያቄዎች የሰጧቸውን መልሶች መነሻ በማድረግ መጪው ጊዜ ካለፈው ይሻል ወይም ይብስ እንደሆነ ትንቢታዊ አስተያየት መሰንዘር፣ አደጋ ካለም ተጠንቅቀን እንድንጠብቅ ማሳሳብ ሲሆን  ሁለተኛው ***ቤን*** አዘጋጀዋለሁ የሚለው ዶኩሜንታሪ ከተራ ፕሮፓጋንዳ ነጽቶ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሃገሪቱን ገጽታ እንዲያንጸባርቅ እንዲረዳው አንዳንድ ነጥቦችን በጥንቃቄ እንዲያይ ማስታወስ፣ እግረ መንገዳችንንም ያለፍርሃት እውነት እንዲናገር ማደፋፈር ነው።

በተረፈ ***ቤን*** አማርኛና እንግሊዝኛ እያደባለቀ ስለተናገረ እርሱ ያለውን እንዳለ ለመድገም ስንል የእንግሊዝኛ ዓረፍተ ነገሮችና ቃላት በመጠቀማችን ይቅርታ እንጠይቃለን።

### *1. የቃለ መጠይቁ የመነሻ ጥያቄዎችና አጠራጣሪ መልሶች፣*

***ቤን*** ብልጠት በተሞላበት ሁኔታ “formally ብዙ ከመሄዳችን በፊት” ይልና የመነሻ ጥያቄዎች ያቀርባል። ጥያቄዎቹ “ምን አይነት አባትና ባል ነዎት? ምግብ አብስለው ያውቃሉ? ምን አይነትና የማንን ሙዚቃ ይወዳሉ?” የሚሉ ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈገግ ብላው “ምን አይነት አባትና ባል እንደሆንኩ መግላጽ ያለባቸው ልጆቼና ባለቤቴ ናቸው” ካሉ በኋላ ከባለቤታቸውም ከልጆቻቸውም ጋር የመቆጣትም የመጋጨትም ችግር አጋጥሟቸው እንደማያውቅ፣ በትጥቅ ትግሉ የመጀመሪያ ወቅት ምግብ ያዘጋጁ እንደነበር፣

እንደስራ ብዙም የሚወዱት እንዳይደለ፤ እንደግዴታም ሆኖ የመጣበት ሁኔታ እንደሌለ፤ በወጣትነት ዘመናቸው ይወዷቸው የነበሩ የውጭም
የሃገር ውስጥም ሙዚቃዎች እንደሚያዳምጡ ገለጹለት። ***ቤን*** በድፍረት ከዘፈኖች ምሳሌ እንዲሰጡት ሲጠይቃቸው በደፈናው "የድሮዎቹ" አሉት። "የእነ ጥላሁን ገሰሰን?" ሲላቸው "የእርሱም የውጭውም" በማለት መለሱለት።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ መልሶች አጫጭር ቢሆኑም ስለ እርሳቸው አንዳንድ ነገሮች ይናገራሉ። ከመነሻው "ምን አይነት አባትና ባል እንደሆንኩ መግለጽ ያለባቸው ልጆቼና ባለቤቴ ናቸው" ያሉት ትክክል ነው። ***ቤን*** የጠቅላይ ሚኒስትሩን ልጆችና ባለቤት እነጋግሮ እንደሆነ ከቃለ መጠይቁ መረዳት አይቻልም። ቢያነጋግራቸው ምን እንደሚሉ የሚገመት ቢሆንም በሚያዘጋጀው ዶኩሜንታሪ ውስጥ ሃሳባቸውን ሲገልጹ ማየትና መስማት እንፈልጋለን። ***ቤን*** እንግዲህ እነዚህን ሰዎች ሳይደነገጥና scared ሳይሆን ማነጋገር ባይዘነጋ ደህና ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከልጆቻቸውም ሆነ ከባልቤታቸው ጋር የመቆጣትም የመጋጨትም ችግር እንዳላጋጠማቸው ቢናገሩም በየአጋጣሚው በትዝብት አምዶች ላይ የተነበቡ ክስታቶች አሉ። የእርሳቸው ወይም የባለቤታቸው ምርጫ ወይም የሁለቱም ስምምነት መሆኑ ባይታወቅም እመቤቲቱ ከማጀት ብቅ ያሉት ባለፉት ጥቂት አመታት ነው። የየሃገሩ መሪዎች በየስብሰባው፤ በየጉብኝቱ ሚስቶቻቸውን (ሴት መሪዎች ደግሞ ባሎቻቸውን) ይዘው ሲጓዙ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ያንን ሲያደርጉ አይታዩም ነበረ። ወቀሳው ሲባዛባቸው ሁኔታውን ለማስተካከል ሞክረዋል። የባከኑትን ዓመታት ለማካካስ በተደረገ ሙከራ ይመስላል እመቤቲቱ በአንድ ጊዜ የሕዝብ ተወካዩች ምክር ቤት አባልና የምክር ቤቱ የሶሻል ጉዳዩች ንዑስ ኮሚቴ ሰባሳቢ ሆኑ። በአህጉር ደረጃም ቢሆን በኤድስ ጉዳይ ከፕሬዚዳንቶችና ጠቅላይ ሚኒስትሮች ባለቤቶች ጋር መታየት ጀመሩ። ከዚያም የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ከሰማንያ በሚበልጡ የገዢው ፓርቲ ሽርክ ኩባንያዎች ስንን ይዞ አላላውስ ያለውን EFFORT በሥራ አስኪያጅነት መምራት ተጨመረላቸው። እመቤቲቱ ሜጋ የተባለ ኩባንያ ለኪሳራ መዳረጋቸው እየታወቀ በምክር ቤት ሥራቸው ላይ ኤድስ እንዲሁም EFFORT ተጨምሮ ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ ሆኖባቸው ቢቸገሩም እስክ አሁን እጅ አልሰጡም። በጠቅላይ ሚኒስትሩና በእመቤቲቱ መካከል የግጭት መከሰት ወሬም በቅርቡ ተናፍሶ ነበረ። የአሜርካው ፕሬዚዳንትና ባለቤታቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩንና እመቤቲቱን ኋይት ሃውስ ጋብዘዋቸው ከግብዣው ሲደርሱ እመቤቲቱ ንዴት ስለታየባቸው ከግብዣው ተገልለው ቆዩ ተባለ። የተናደዱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጎነጥ አድርገዋቸው ነው የሚልም ወሬም ተነዛ። ሰውየው እንደሚሉት ግጭት ኖሯቸው የማያውቅ ከሆነ የተባልው ሁሉ ፈጠራ ነው ማለት ነው። ***ቤን*** ልብ ካለው ይህንንም አጣርቶ ይነግረናል።

በቅርቡ ከልጆቻቸው አንዷ ቢሾፍቱ ላይ ክላሽንኮቭና ሽጉጥ ይዛ ኢላማ ስታፈላልግ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሞቅ ብሏት ከብዙ ወጣቶች ጋር ስትዳራ የሚያሳዩ ፎቶግራፎች በየድረ ገጹ ተሰራጭተው በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሰው አይቷቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ንዴት ገብቷቸው አልተቆጧትም? ይህን ካላደረጉ መቼም የሚገርም ነገር ነው። ***ቤን*** ልጅቷን ስለአባቷና እናቷ ግንኙነት፤ እርሷና እህቶቿ ከአባታቸውና ከእናታቸውጋር ስላላቸው ግንኙነት ጠይቋት ቢያቀርብልን የሚሰራውን ዶኩሜንታሪ ምንኛ የታሚላ ባደረገው? እውነት ሰውየው እንደሚሉት ተጋጭተውም ተቆጥተውም የማያውቁ ከሆነ አንድም ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋር አይገናኙም፤ ሁለትም እርሳቸው የሚያውቁት ግጭት ጦርነት ብቻ ነው፤ ሦስትም ባለቤታቸውና ልጆቻቸው ጥፋት አይፈጽሙም፤ አራትም እርሳቸው ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን አያናድዱም ማለት ነው። አንዳቸውም አማራጮች ጤናማ የቤተሰብ ግንኙነት አያመለክቱም። አሁን እውነት በህዝብ ህይወትና ነጻነት ላይ ያለአንዳች ርህራሄ በማናቸውም መለኪያ ጭካኔ ነው የሚባል ተግባር የሚፈጽሙ ሰውዬ

ከልጆቹና ከባለቤቴ ጋር ተጋጭቼም ተቆጥቼያቸውም አላውቅም ቢሉ የሚያምናቸዋል ሰው አለ? ባለቤታቸውና ልጆቻቸው ጭካኔያቸውን ስለሚያውቁ እየፈሩ ፊታቸው የማይቆሙ ከሆነ ግጭቱ ላይኖር ይችል ይሆናል። እኛ በምንኖረበት በገሃዱ ዓለም ግን ያለግጭት የሚኖር ቤተሰብ የለም። እንደማናቸውም ሰው አንዳንዴ ቁጣም ግጭትም አለ፤ ነገር ግን ለጉዳት አልሰጠንም ቢሉ ይሻል ነበረ። *ቤን* ይሄን ነገር ማጣራትና ዶኩሜንታሪው ውስጥ መጨመር አለበት እንላለን። ጉዳዩ የጠቅላይ ሚኒስትሩን የግል ህይወት የሚመለከት ቢሆንም ህዝብ እውነቱን የማወቅ መብት አለው። የሃገር መሪ በግሉ የሚመራው ህይወት እንዳይታወቅ መከላከል፤ መደበቅም ሆነ መዋሸት አይገባውም።

የሙዚቃውም ነገር እንዲሁ አጠራጣሪ ነገር አለበት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከውጭ ዘፋኞች በስም አንስተዋት የሚያውቋት ቲና ተረነር ናት። እርሷን ያነሱት በአንድ ወቅት “What’s Love Got to do With It?” የሚለው የዘፈኗ ርዕስ ለፖለቲካ ንግግር ይበልጥ ገላጭ መስሎ ስለታያቸውና ስለተጠቀሙበት ነው። ወይዘሮ ተርነር ታዋቂ የፖፕና የሮክ አርቲስት ስትሆን ዘፈኑን ያወጣችው በ 1984 ላይ ነው። ዘፈኑ ከአምስት መቶ ምርጥ ዘፈኖች ውስጥ አንዱ በመሆን እንዲሁም ባለፈው ክፍለ ዘመን ከወጡት ዘፈኖች ውስጥ ሰላሳ ስምንተኛ በመውጣት ተውዳጅነቱን አስመስክሯል። ባጭሩ የተዋጣለትና ብዙ የተሸጠ ዘፈን ነበረ። ዘፈኑ በወጣበት ወቅት ወጣት የነበረ ሁሉ እንደወደደው ጠቅላይ ሚኒስትሩም ከመውደዳቸው በስተቀር ዘፈኑ ለእርሳቸው ልዩ ትርጉም እንዳለው ያስረዱበት አጋጣሚ የለም። የጥላሁን ገሰሰን ስም ያነሳባቸው *ቤን* ራሱ ሲሆን እርሳቸው ስሙን እንኳን ደግመው ሳይጠሩ “እሱንም” አደምጣለሁ በማለት ያልፉታል። ነፍሱን ይማረውና ጥላሁን ሃገር ወዳድ ስለነበረና በብዙ ዘፈኖቹ ይህንኑ ስላንጸባረቀ ሰውየው ዘፈኖቹን በፍቅር ያዳምጣሉ የሚል ግምት የለንም።

ከላይ ያነሳናቸው የመነሻ ያልናቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው እግረ መንገዳችንን ዳሰስናቸው እንጂ ትኩረታችን ሌሎቹ ጥያቄዎችና መልሶች ላይ ነው።

## *2. የጠቅላይ ሚኒስትሩ የተዛባ የምልከታ አቅጣጫ፤*

ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በድርጅታቸውና በመንግስታቸው የተሰጡ ውሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃዎች ወይም በተቃራኒው መወሰድ ሲኖርባቸው ሳይወሰዱ የቀሩ እርምጃዎች ሃገራችን ዛሬ ያለችበት ሁኔታ ላይ እንድትገኝ አድርገዋል። ዛሬ የሚሰጡ ውሳኔዎችና የሚወሰዱ እርምጃዎች የዛሬ አስር ዓመት፤ ሃያ ዓመት፤ ሃምሳ ዓመት እንዲሁም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ሃገራችን የምትገኝበትን ህኔታ ይወስናሉ። ውሳኔዎቹና እርምጃዎቹ ጥሩ ከሆኑ ጥሩ ቦታ መጥፎ ከሆኑ ደግሞ መጥፎ ቦታ ያደርሳሉ። በየግል ህይወታችን ካየናቸው ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ዛሬ ካለን የተሻለ ወይም የባሰ ሃገር እንዲወርሱ፤ እስከ ጭራሹ ሃገር የሚባል ነገር እንዳይኖራቸው ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

በደርግ ጊዜ የንጉሱ ዘመን ይሻል ነበር የሚሉ በርካታ ሰዎች ነበሩ፤ አሁንም አሉ። ከአስራ ስምንት ዓመታት በኋላ በስልጣን ላይ ያሉትን ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ድርጅታቸውንና መንግስታቸውን ከደርግ መሪ፤ ድርጅትና መንግስት ጋር አወዳድረው የደርግ ጊዜ ይሻል ነበረ የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። እንደዚህ የሚሉት የርዕዮተ ዓለም ታማኝነት (loyality) ይዟቸው ወይም የስርዓቱ ተጠቃሚ ስለነበሩ ሳይሆን እንዲያው ያዩትንና የመሰላቸውን መናገራቸው ነው። በጅምላ አንዱ መሪ፤ ድርጅት ወይም መንግስት ከሌላው ይሻላል ማለት አስቸጋሪ ቢሆንም ተናጠል መለኪያዎች አውጥቶ ማወዳደር ግን ይቻላል። ቢሆንም እዚህ ማድረግ የምንፈልገው ያለፉትንና አሁን ያሉትን መሪዎች፤ ድርጅቶችና መንግስታት ማወዳደር ሳይሆን የበፊቱን መሪ፤ ድርጅትና መንግስት የተኩት የአሁኑ መሪ፤ ድርጅትና መንግስት (ስልጣን ላይ መቆየታቸው ካልቀረ) ወደፊት ሥልጣን ላይ የሚቆዩባቸው

ዓመታት ካለፉት በእጅጉ የተሻሉ መሆን እንዳለባቸው አጽናኦት ለመስጠት ነው። በተለይም ያለፈውን በማውገዝ አልፎ ተርፎም በማስወገድ ሙሉ ሃላፊነት የተረከቡ ስልሆነ ካለፈው የተሻለ ውጤት የማስመዝመዝገብ ግዴታ ነበረባቸው። ያ ግዴታ አሁንም ከአስራ ስምንት ዓመታት በኋላ አለ። ልዩነቱ ግዴታው ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ግዙፍ እየሆነ መምጣቱ ብቻ ነው።

የመጪውን ትውልድ ህይወት ከዛሬው የተሻለ በማድረጉ ህዝብ ድርሻ ቢኖረውምታሪክ በበኩሉ የመሪዎች ድርሻ ከህዝብ ድርሻ የበለጠ ወሳኝነት እንዳለው በተደጋጋሚ አሳይቷል። እንዲያው ልማድ ሆኖ "ታሪክን የሚሰራው ህዝብ ነው" ይባላል እንጂ ታሪክን የሚሰሩት መሪዎች ናቸው።  እንደኛ ባለ ሃገር ህዝብ ወቅት እየጠበቁ በሚካሄዱ ምርጫዎች ከመሳተፍ ውጪ የፖለቲካ መብትም ሆነ ተሳትፎ እንዳለው አጠያያቂ እየሆነ መጥቷል። አንዳንዶች ህዝብ እንደፖለቲካ category መኖሩንም መጠራጠራቸውን በየአካዳሚክ ውይይቱ ያነሳሉ። የሃገራችንን ያለፈ አንድ መቶ አመታት ታሪክ ብቻ ወስደን የህዝብንና የመሪዎችን ድርሻ ብንመርምር በበጎም ሆነ በማጥፎ ሁኔታዎች የመሪዎች ድርሻ ወሳኝ እንደነበረ ማረጋገጫዎች በገፍ እናገኛለን።

ዛሬ ሃገራችን የምንላትን ያሰባሰቡት አጼ ምኒልክ ናቸው። ንጉሱ እንደ እኛ አቆጣጠር ከ 1870 ቹ እስከ 1890 ቹ ባሉት ዓመታት ወታደርዊና ሌሎች መንገዶች በመጠቀም በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ እንዲሁም በመሃል ሃገር የራስ አስተዳደር የነበራቸውን ህዝቦች እርሳቸው ይመሩት በነበረው መንግስት ስር አስገቡ። የአጼ ሃይለ ሥላሴ፣ የደርግ እንዲሁም ያለው መንግስት አጼ ሚኒሊክ ያሰባሰቡትን ሃገርና ህዝብ በወራሽነት ተረክበው አሁንም ያስተዳድራሉ። አጼ ምኒሊክ አዲስ ሃገር በመፍጠር ብቻ ሳይወሰኑ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን በማቋቋም የሥራ ክፍፍልና ሃላፊነትን ያስተማሩ፣ ከውጭው ዓለም ጋር ግንኙነት በመፍጠር ንግድ እንዲስፋፋ ያደርጉ፣ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌፎንና የባቡር ሃዲድ በመዘርጋት ዘመናዊ አገልግሎት እንዲጀመር ፈር የቀደዱ፣ የጤናና የትምህርት ቤቶች በማቋቋም የህዝቡ ኑሮ እንዲሻሻል የጣሩ መሪ ናቸው። አጼ ሃይለ ሥላሴም ቢሆኑ አጼ ሚኒሊክ በጀመሩት ላይ በማከል የራሳቸውን አስተዋጻኦ አድርገዋል።  ከእነዚህ ውስጥ ሃገሪቱን የመንግስታት ሊግ አባል ማድረግ፣ ህገ መንግስቶችን ማውጣት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ማዋቀር፣  የፓርላማ አባላት ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ፣ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መክፈትና ማስፋፋት፣ ወጣቶችን ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ መላክ፣ የህትመት ሥራን ማስጀመር፣  የዘመናዊ የህክምና ቤቶችን ማስፋፋት፣ መንገዶች መስራትና የራዲዩና የቴሌቪዥን አግልግሎቶችን ማጀመር ሊጠቀሱ ይችላሉ። ደርግም ቢሆን ከቀዳሚዎቹ መሪዎች የተረከበውን ሀገርና ህዝብ ሳይበታተን ለማቆየት ሲል መገንጠል ከሚፈልጉ የብሄር ታጣቂ ንቅንቄዎችና ከሱማሊያ መንግስት ጥቃት በመከላከል፣ አዲስ ህገ መንግስት በማውጣት፣ ዙፋናዊነትን እንደመንግስት ስርአት በማስቀረትና ሪፐብሊክ በማቆም፣ መሬትን የመንግስት በማድረግና የአርሶ አደሮችን የመጠቀም መብት በማረጋገጥ፣ የግል ፋብሪካዎችንና የአገልግሎት ተቋሞችን በመውረስ አሁን ስልጣን ላይ ላለው መንግስት ዳጎስ ያለ ገቢ ትቶ ሄዷል። አሁን ያለው መንግስትም የሃገሪቱን አንድነትና ጥቅሞች በማስጠበቅ ጉዳይ ብዙ ባይታመንም የቀዳሚዎቹ መንግስታት በጀመሩት የልማት ሥራ ገፍቶበታል።

ከለይ ባጭሩ የቀረቡት ባለፉት መቶ ዓመታት በሃገርችን ስልጣን ላይ የነበሩ መሪዎችና መንግስቶቻቸው ያደረጉትን "በጎ" አስተዋጽኦ ሲሆን በማወቅም ይሁን ባልማወቅ ወይም በአቅም ማጣት ምክንያት ያወረሱን ጎጂ ሁኔታዎችም አሉ። አጼ ምኒልክ ጣልያን ኤርትራን ለቆ እንዲወጣ በሁሉም መስክ ጥረት አለማድረጋቸው፣ አፄ ሃይለ ስላሴ ከኤርትራ ጋር የነበረውን ፌደሬሽን አፍርሰው ኤርትራን አስራ አራተኛ ክፍለ ሃገር ማድረጋቸውና በኋላም ክፍለ ሀገሩን በወታደራዊ አስተዳደር ስር ማስገባታቸው፣ ደርግ

ደግሞ ከብሄርተኞቹ ጋር በሦስተኛ ወገኖች አማካይነት ወይም በቀጥታ ለመነጋገር ፍላጎት ቢያሳይም ለወታደራዊ መፍትሄ ትኩረት በመስጠቱ፤ አሁን ስልጣን ላይ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትርና መንግስታቸው ደግሞ ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ ያለአንዳች ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቂያ በተለይም ድንበርንና ወደብን በሚመለከት ምንም አይነት ድርድር ሳያደርጉ የኤርትራን "ነጻነት" በማጽደቃቸው ህዝቡ ድንበር ለማስከበር በህይወቱና በሃብቱ መስዋዕትነት እንዲከፍል አስገድደውታል። አማራጭ ወደብም አሳጥተውታል።

አጼ ምኒሊክ ከሱዳን ጋር ያለንን ድንበር በሚመለከት ከእንግሊዞች ጋር በ 1902 እን 1907 ስምምነቶች ቢያደረጉም ስምምነቶቹን ተከትለው በ 1903 እን 1909 የተካሄዱ የድንበር "ማካለሎች" ሃገራችን ያልተሳተፈችባቸው መሆኑ እያታወቀ፤ የአጼ ሃይለ ስላሴና የደርግ መንግስት ከሱዳን ጋር ያደረጓቸው የደብዳቤ ልውውጦችና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች በድንበር ጉዳይ ለሱዳን በፊት ከነበረው በተጨማሪ ያስገኘው ነገር ሳይኖር ጠቅላይ ሚኒስትሩና መንግስታቸው በድጋሚ ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ መሬታችንን አሳልፈው ለመስጠት ላይ ታች ይላሉ። ከጥቂት አመታት በፊት በህዝብ መራራ ተቃውሞ ምክንያት የተቋረጠው የድንበር ማካለል ስራ ከመጪው የፌደራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በኋላ ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሱዳን ጋር ድንበር ለመካለል የተጣደፉበት ምክንያት አይታወቅም። የአጼ ሚኒልክ፤ የአጼ ሃይለ ስላሴና የደርግ መንግስታት የሃገሪቱን ጥቅም ሙሉ ለሙሉ ለማስጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ የመደራደርም ሆነ የድንበር መካለል አቅም እስኪጎለብት ድረስ የሃገሪቱን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ላለመስጠት እያስተላለፉ ያቆዩትን ድርድር እንደድክመት በማቅረብ ደፋርነታቸውን ለማሳየት  አይናቸውን ጨፍነው ገብተውበታል።

እነዚህ ምሳሌዎች መሰረታዊ የሃገር ህልውናና ጥቅም ጉዳዩች ስልጣን ላይ በነበሩ፤ አሁንም ባሉ መሪዎች የሚወሰኑ እንጂ ህዝብ ወይም እውነተኛ የህዝብ ተወካዩች ምንም ድርሻ እንዳልነበራቸው - አሁንም እንደሌላቸው ፤ ድርሻ ቢኖራቸውም እጅግ አናሳ እንደሆነ ያመለክታሉ። ከላይ እንዳየነው በሁለቱ አጼዎችም ጊዜ ሆነ በተከታዩቹ ሁለት ፈላጭ ቆራጭ አስተዳደሮች ህዝብ በኤርትራም ሆነ በሱዳን ጉዳይ በቀጥታ ራሱ ወይም በእውነተኛ ተወካዩቹ አማካይነት በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ግልጽ፤ ነጻና በቂ ውይይት አድርጎ ውሳኔ አላሳለፈም። አፈጻጸማቸውንም አልተከታተለም ወይም የሚከታተሉለት አልመደበም ። ነገር ግን መሪዎቹ በዘፈቀደ በሚወስዱት ውሳኔ እየተገደደ አንጡራ ሀብት ንብረቱን ይቀማል። መሪዎቹ ግፉ ቢል በታሪክ ሲወቀሱ እንጂ በጥፋታቸው ሲጠየቁ አይታይም። ወደፊትም የሚጠየቁ አይመስልም።

ባለፉት ብዙ ዓመታት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የእይታ አቅጣጫ በእጅጉ የተዛባ ነበረ። ከላይ እንደተባለው በኤርትራም ሆነ በሱዳን የድንበር መካለል ጉዳይ የወሰዱዋቸው አቋሞች ሀገሪቱንና ህዝቡን በከፍተኛ ደረጃ የጎዱ ናቸው። በኤርትራ ጉዳይ የህግ አስገዳጅነት ያለው የግልግል ስምምነት ከፈረሙ በኋላ የግልግሉ አካል የሰጠውን ውሳኔ ወደጎን አድርገው ከህግና ከውሳኔው ውጭ "ሰጥተን እንቀበል" በማለት ሙጭጭ ብለዋል። በስምምነቱ መሰረት የተሰጠው ውሳኔ እንዳለ እንዲፈጸም ስምምነቱም የዓለም አቀፍ ህግም ያስገድዳሉ። በኤርትራ በኩል መለሳለስ ተደርጎ ሰጥተን እንቀበላለን ካላሉ (ለነገሩ የሚሉ አይመስሉም) የማታ ማታ የተወሰነላቸውን ማግኘታቸው አይቀርም። ባለው ሁኔታ እስከተወሰነ ደረጃ ራሷ ኤርትራም ተጎጂ ብትሆንም ድርብ ድርብርብ ተጎጂዎች የምንሆነው እኛ መሆናችን አያጠራጥርም። በጉልበት የያዝነውን መሬት በመጨረሻ እንለቃልን። እስክንለቅ ድረስ ድንበር አካባቢ ለሰፈሩት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች ደሞዝ፤ አበልና ለሚይዙት መሳሪያ ከፍተኛ ወጪ እናደርጋለን። ጊዜ ሳናጠፋ በአማራጭ ወደብ በመጠቀም የኪራይ ክፍያ መቀነስ አንችልም። የወደብ ጥገኝነታችንን መነሻ አድርጋ በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ ከምትገባ አናሳ የጎረቤት ሃገር አንገላገልም። በድንበር አካባቢ በንግድ መጠቀም

አንችልም። ድንገት የተቋረጠውን የታሪክ፣ የባህልና የሶሻል ግንኙነቶች መጠገን አይታሰብም። ዘላቂ ጠላት በማበራከት ሃገሪቱን እናስከብባልን።

የሱዳን ነገርም ሲነሳ የድንበር መካለል ድርድር የተጀመረው ለኛ በማይጠቅምበት ጊዜ ነው። አቅማችን በደከመበት ወቅት ድርድሮችን ማስተላልፍ ባልጎዳም ነበር። ሱዳን በቅርቡ ባገኘችው የነዳጅ ሃብት ምክንያት የኢኮኖሚ አቅሟ በመጎልበቱ ከሃገራችን ጋር ያላትን ግንኙነት በበላይነት እየመራች ወደምትፈልገው አቅጣጫ መውሰድ ችላለች። በድንበር ጉድይ ብቻ ሳይሆን በአባይ ውሃ ድርሻና አጠቃቀም ድርድር ወቅት የሱዳን የበላይነት በሰፊው ተንጸባርቋል። ሱዳን ያለችበት ሁኔታ ሃገራችንን ማሸከርከር የማያስችላት አልነበረም። ወደ ሃገራችን ነዳጅ ትልካለች። ያሏትን ወደቦች ለሃገራችን ክፍት አድርጋለች የሚል ወሬም ተናፍሶ ነበር። ያለውን መንግስት በትጥቅም ሆነ በሌላ መንገድ የሚፈታትኑ ሃይሎች በሱዳን በኩል እንዳይግቡ ለማድረግ እንደምትችል በተግባር አሳይታለች። ከሃገራችን የኤሌክትሪክ ሃይልና ሌሎች ምርቶች ለመግዛት የተስፋ ቃል ሰጥታለች። በወታደራዊ፣ በዲፕሎማሲያዊና በጸጥታ ጉዳይ ከሃገራችን ሙሉ የመደጋገፍ ስምምነት አድርጋለች። በአንጻሩ ከሃገራችን የምትፈልገው የድንበሩን መካለል ብቻ ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ አሁን ስልጣን ላይ ካሉት ጠቅላይ ሚኒስትር የበለጠ ሃገሪቱንና ህዝቡን የጎዳ ድርጊት የፈጸመ መሪ የለንም። ያለውም ሆነ መጪው ትውልድ እርሳቸውና የሚመሩት መንግስት በሚያደርጋቸው ስምምነቶች ሁሉ ተገዳጅ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። ከዚህ ሌላ ለሃገሪቱ ሰላምና ልማት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዩችን ለምሳሌ በህገ መንግስቱ የተረጋገጡ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች አለመከበርን፣ የፍትህ አካልትን ገለልተኛነት ማሳጣትን ፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች መሳደድን እና የነጻ ጋዜጠኞችን እንግልቶሽ ስንወስድ ጎጂ ባህርያቸውና ድርጊታቸው ይበልጥ እየጎላ ይመጣል።

***ቤን*** ላቀረበላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች የሚያንጸባርቁት ይህን ጎጂ ባህሪያቸውንና አሰራርቸውን ለመቀየር ዝግጅቱም ፍላጎቱም እንደሌላቸው ነው።

*3. The New Face of Ethiopia*

***ቤን*** "እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ሰው ሲሰክር ፖለቲካ ያወራ ነበር። ... አሁን ሳይሰክር ሲናገር አይቻለሁ።ይሄ ነገር ያስደስተኛል። አንዳንድ ልማቶችም አያልሁ" በማለት የማበረታቻ ንግግር ካደረገ በኋላ የመጀመሪያ ጥያቄውን ያቀርባል። ጥያቄው " "The new face of Ethiopia" በእርስዎ እይታ ምንድነው ብለው ያስባሉ?" የሚል ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲስ ያሉትን የኢትዮጵያ ገጽታ እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> "ከረዥም ጊዜ ከፊል እንቅልፍ በኋላ ከእንቅልፍ ባንኖ መጀመሪያ እንደማንኛውም
> ከእንቅልፍ የነቃ ሰው የመወራጨት አዝማሚያ ነበረው። በሂደት በይበልጥ እየሰከነ
> አካባቢውን እያወቀና እየተረጋጋ መራመድ የጀመረ ህዝብና ሃገር ነው ብዬ ነው
> የምወስደው።
> በሁሉም አቅጣጫ - በልማቱም፣ በዲሞክራሲውም፣ እንዳልኩት ከእንቅልፉ የነቃ
> ሃገርና
> ህዝብ ስለሆነ (ከረጅም እንቅልፍ በኋላ) በመጀመሪያ ሲነቃ እንደሚያጋጥመው
> ሁሉ የተወሰነ
> የመደናበር ሁኔታ ቢኖር የሚገርም አይደለም። በሂደት ግን በደንብ እየሰከነና
> እየተረጋጋ

*መራመድ የጀመረ ህዝብ አድርጌ ነው የምወስደው።"*

*ይህን መልስ በሁለት ክፍሎ መመልከት ያስፈልጋል። አንደኛው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቃለ መጠይቁ ወቅት ለስምንት ጊዜ ያነሱት የህዝቡና የሃገሪቱ ረጅም እንቅልፍና ከእንቅልፍ የመንቃት ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው ህዝቡ እየሰከነ፤ አካባቢውን እያወቀና እየተረጋጋ መራመድ የመጀመሩ ጉዳይ ነው።*

### *3. 1. " ከረጅም ጊዜ ከፊል እንቅልፍ በኋላ ከእንቅልፍ ባንኖ ..."*

*እንቅልፍ ሲያንስም ሲበዛም ችግር ስለሆነ በጤና ባለሙያዎች ይጠናል። እንቅልፍን ያጠኑ ተማራማሪዎች ጤነኛ ሰው የእድሜውን አንድ ሶስተኛ ተኝቶ ያሳልፋል ይላሉ። ስለአንድ ህዝብ ለረጅም ጊዜ በእንቅልፍ ላይ መቆየት ሳይንቲስቶች ያደረጉት ጥናት እንዳለ አናውቅም። በተለምዶ ግን ለረጅም ጊዜ ያንቀላፋ ማለት ለውጥ ውይም መሻሻል ያላሰየ "ባለበት የሚረግጥ" እንደማለት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሌላ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ " ረጅምእንቅልፍ" ወዳሉት ሃሳብ ቢመለሱም  ምን እንደሆነ አያብራሩትም። ግን አገላለጹን እንደገና ይጠቀሙበታል።*

*"ይሂ ህዝብ በአንድ ወቅት በአለም ከሰለጠኑት ታላላቅ ስልጣኔዎች አንዱ የነበረ ሲሆን ለብዙ*
*መቶ አመታት በተለያዩ ምክንያቶች አንቀላፍቶ እንደነበር ሊገመት ይችላል። ሁኔታው ይሂ*
*አንቀላፍቶ የነበረ ህዝብ ከእንቅልፉ የባነነበትና መራመድ የጀመረበት ነው። ... ስለዚህ*
*ከእንቅልፍ የባነነ ህዝብ እና ከእንቅልፍ ሲነቃ የነበረው የተወሰነ መደናገጥ የተሻገረ ህዝብ*
*ተረጋግቶ፤ ሰክኖ መራመድ ሲጀምር የሚታየው ነው። አዲስ ነገር ሳይሆን ተኝቶ የነበረና የነቃ*
*ሰክኖ ወደፊት መራመድ የጀመረ ህዝብ ነው ብዮ ነው የማስበው።"*

*ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመጀሪያው ክፍል የተናገሩት ስለአክሱም ስልጣኔ እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለታሪካዊው የአክሱም ስልጣኔ እዚህ ማተት ቦታው ባይሆንም ስልጣኔው ካከተመ ቢያንስ ሺህ አመታት አልፈዋል። የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪዎች የአክሱም ስልጣኔ ያከተመው ከእስልምና መስፋፋት ጋር በተያያዘ በቀይ ባህር ላይ የነበረው ይዞታና የበላይነት እያተደካመ በመምጣቱ፤ በአዶሊስ ወደብ ላይ በደረሰ ወታደራዊ ጥቃት ወደቡ ለንግድ የነበረው ጠቀሜታ በመቀነሱና ሁኔታው ሩቅ የነበሩ ወደቦችን መጠቀም በማስገደዱ፤ በአካባቢው በተነሳው የቤጃዎች አመጽ እና ወታደራዊ ስራዎች በመቀዝቀዛቸው በይበልጥም እርሻ በመዳከሙ እንደሆነ ይናገራሉ። የአክሱም ስልጣኔ ካከተመ በኋላ የመንግስት መቀመጫ በዛጉዌ አገዛዝ ወደ ላሊበላ ተወስዶ የሰሎሞናዊ ነገድ  እንደገና ስልጣን ከቀማበት* 13 *ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በቅርቡ እስኪወገድ ድረስ የዙፋናዊ አገዛዝ አንሰራፍቶ ቆየ። እንደ አውሮፓ የ* mercantile order *እንዳይስፋፋና በኋላም የካፒታሊስት ስርአት እንዳይፈጠር ፊውዳልዊው ዙፋናዊ አገዛዝ ከመኳንንትና መሳፍንት እንድሁም ከጦር አብጋዞች ጋራ በመተጋገዝ* imperial order *በመዘርጋት ህዝቡን አላላውስ ብለው ያዙት። እስልምና የባህር በር በመዝጋት ዋነኛውን የንግድ ኬላ በመቆጣጠር የህዝቡን* enterprenurial spirit *እንዳያንሰራራ አድርጎ ደቆሰ። የኦርቶዶክስ ክርስትና ደግሞ ከገዢዎች ጋር በመሰለፍ የህዝቡን ስነ ልቦና በማኮላሸት ነጻ የፖለቲካም ሆነ የፍልስፍና ባህል እንዳያሳድግ ገትቶ ለዘለአለም ተገዢነት ዳረገው። እስልምናና ክርስትና ምንም አይነት ምክክር ሳያደርጉ በተናጠልና በጣምራ* ritual order *መሰረቱ።*

እንግዲህ በ imperial order እና በ ritual order ስር በአስቸጋሪ ሁኔታ የኖረውን ህዝብ ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ "እንቀላፍቶ ነበር" ያሉት። ችግሩ ግን ለእንቅልፉ ተጠያቂ ማነው የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ነው። ከፍ ብሎ እንዳየነው የአክሱም ስልጣኔ ያከተመው የባህር በርና የወደብ ማጣት በንግድና ወታደራዊ ስራዎችን ላይ ያስከተሉት ጫና፤ የህዝብ አመጽና የእርሻ መዳከም ናቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህዝቡ ከእንቅልፉ ነቅቶ መራመድ ጀምሯል ቢሉም አክሱምን ያሽመደመዱና ለታሪክ የዳረጉ ችግሮች በከፊል እርሳቸውና መንግስታቸው በፈጸሙት ጥፋት የተነሳ ዛሬ አብረውን አሉ። ወደብ የለንም። ወደብ በማጣታችን ርካሽ የሆነውን የባህር መጓጓዣ የመጠቀም አቅማችን በእጅጉ ተዳክሟል። በዚያውም መጠን ንግድ በሚፈለገው መጠንና በርካሽ ዋጋ ማካሄድ አልተቻለም። ከዚህም የተነሳ ህዝቡ ተጎድቷል። በፍርሃት በአደባባይ ወጥቶ አልተናገረም እንጂ በዝምታ አዝኗል። የወደብ ችግር ያስከተለውና ወደፊትም የሚያስከትለው የኢኮኖሚ መዘዝ እያለ ፋይዳ ያለው እርምጃ ማድረግ ዘበት ነው። በዚህ ምክንያት ከእንቅልፉ ነቃ ያሉት ህዝብ እውነት ነቅቶ ከሆነ እንደአክሱማዊው ተመልሶ ማሸለቡ አይቀርም። ከአክሱም ማክተም በኋላም ህዝቡ ወደፊት እንዳይራመድ ቀፍደደው የያዙት የማእከልና የክልል መንግስታትና አገልጋዩቻቸው ነበሩ። እነዚህ ተቋማት ዛሬም አብረውን አሉ። በፊት ያካሂዱ የነበረውን ድርጊት ዛሬም በሰፊው ተያይዘውታል።

በቅርቡ አንድ ምሁር "ኢትዩጵያ የአሰብ ወደብን የመጠቀም መብቷን ያጣችው በፓርቲው ውስጥ በነበረው ድንቁርና እና ትእቢት ነው" ብለዋል፤ መልስዎ ምንድነው ተብለው ለተጠያቂት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲመልሱ በሙያው እውቅ የሆኑ የህግ ምሁራን የመከሩንን ነው ተግባራዊ ያደረግነው፤ ጥፋቱ የኛ አይደለም በማለት ጥፋታቸውን ወደ ሌሎች ማስተላልፍ ሞክረዋል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለኤርትራ "ነጻነት" ተጋድለናል፤ መገንጠላቸውንም እንደግፋልን ሲሉ የነበሩ ሰውዬ ዛሬ የህግ ምሁራን የመከሩንን ነው ተግባራዊ ያደረግነው ይበሉ? የህግ ምሁራን የተባሉት "ጥቁር ነጭ ነው" ብለው ሲያስተምሩ፤ ሲጽፉና ሲናገሩ የኖሩ፤ በሺህ የሚቆጠሩ አፈ ጮሌና ቀጣፊ ጠብቆች በዚህ "ጥቁር ነጭ ነው" ሙግት አሰልጥነው ህዝብ መሃል ያሰማሩ አጥፊዎች ናቸው። የሰዎቹ ማንነት እየታወቀ የሚነግሯቸውን ሰምተው ሃገር ያለወደብ ያስቀራሉ? ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉትን ለማንበብ በቅርቡ "የታጠቁትንም ያልታጠቁትንም ሃይሎች እያተከታተልን ነው" በሚል ርእስ ዲሴምበር 16/ 2009 በሪፖረተር ላይ የወጣ ጽሁፍ ይመልከቱ። ይሄ ጥፋትን ወደ ህግ ምሁራን የማስተላለፍ ሙከራ እውነትም ሆነ ውሸት ወደቡ ያላግባብ መታጣቱን የማመን ያህል ነው።

የወደብ ማጣት በንግዱ ላይ የፈጠርው ግዙፍ ጫና እንዳለ ሆኖ ሃገሪቱ ለኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ የሆነውን የነጻ ገበያ መሰረት mercantile order ለመፍጠር መሰረት አልጣለችም። የተወሰኑ መስኮች አሁንም ለመዋዕለ ንዋይ ፈሰስ ዝግ ናቸው። የሚደረግውም መዋዕለ ንዋይ በጠብታ አይነት እንጂ በመንቆርቆር የሚወርድ አይደለም። አንዳንዱም መዋዕለ ነዋይ (ለምሳሌ በቅርቡ በገፍ ለዓለም ዓቀፍ ካቲታል የተጋለጠው የእርሻ መሬት) ጠቅሚታው በበቂ ሁኔታ ሳይገመገም የሚካሄድ ነው። የጥቅሙ አራማጅ መደብም mercantile calss እንዳይፈጠር በአርሶ አደሩ ርዕዩተ ዓለም ታሽቶ የቀረበው ግብርና መር ኢኮኖሚ አፍኖ ይዞታል። በፈርቃ ስልጣን የሚወስዱ elites የዚህ ኢኮኖሚ ፖሊሲና ርዕዩተ ዓለም አራማጆች ሆነው ብቅ ካሉ ዓመታት ትቆጥረዋል። እነዚህ elites በፖለቲካ ፓርቲ ተደራጅተው በወታደራዊና በትምህርት ተቋማት ሳይቀር ደጋፊዎች በማበራከት ስለ ህዝብና ሃገር ጥቅም እያወሩ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን አልፎ ተርፎም የብሄሮቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ሳያሰልሱ ይሰራሉ። ያለ mercantile class ጠንካራ መሰረት ያለው ኢኮኖሚም ሆነ የዲሞክራሲ ስርዓት ለመመስረትም ሆነ ለዘለቄታው እንዲቆይ ለማድረግ ቁሳዊ መሰረት እንደሚጎድል ያውቃሉ። ዛሬ በሃገራችን በተጨባጭ የምናየው ይህንኑ ነው።

አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ አሁን ያሉበት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የሶሻል፣ ወታደራዊ ወዘተ. የእድገት ደረጃ በአስራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ብቅ ባለው mercantile order ማእቀፍ ውስጥ የነበረ አሁንም ያለ ነው። እስከ አሁን በአጥጋቢ ሁኔታ የሰራው በአርሶ አደሩ ርዕዩተ ዓለም ታሽቶ የቀረበው ግብርና መር ኢኮኖሚ ወደፊት ብዙ መግፋት ባይችል የገገርው ፓርቲ በአማራጭም ቢሆን ተዘጋጅቷል። ሁኔታው ሲጠይቅ EFFORT ን ብቅ አድርጎ mercantile class እኔ ስልሆንኩ ተከተሉኝ ማለቱ አይቀርም። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የ EFFORT ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ሰውዬ በሃገሪቱ ካፒታሊዝም ገንብተን እናስረክባልን ሲሉ ተደምጠዋል። መከራከሪያው ስልጣን ላይ ለመቆየት ይረዳል በሚል የቀረበ መሆኑ አያጠያይቅም። ይሄም ካልረዳ ሌላ ሶስተኛ አማራጭ አለ። አመራጩ ለልማትና ለእድገት የአውሮፓው ሞዴል በግድ መከተል አያስፈልገንም፣ የቻይና እድገት ሞዴል ጥሩ አማራጭ ነው የሚል ነው። ችግሩ ግን ፓለቲካንና ኢኮኖሚን በመለያየት ህዝብ ልማትና እድገት ካገኘህ ፖለቲካውን እርሳው የሚባል እንዳይደለ የራሷ የቻይና የቅርብ ጊዜ ልምድ አሳይቷል። ቻይና በፖለቲካው መስክ በተለይም በዲሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች መከበር መሰረታዊና ፈጣን ለውጥ ካላመጣች ከአስርና አስራ አምስት ዓመታት በኋላ ስርዓቱ በአፍጢሙ እንደሚደፋ በርካታ ጥናቶች ያሳያሉ። በሃገርችን ስልጣን ላይ ያለው መንግስት የቻይናን እድገትና ልማት እንደሞዴል ወስዶ "የልማት መንግስት ነኝ"፣ ምርጫ እንዲካሄድ ብፈቅድም ኢኮኖሚውን ስለማለማና ስለማሳድግ ስልጣን ላይ ለዘላልም ልቆይ፣ አትንኩን ማለት ከጀመረ ሰንብቷል። ልማትና እድገት ግን በራሱ በቂ ሆኖ የህዝብን ፍላጎት አያሟላም።
ባጭሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ድርጅታቸውና መንግስታቸው ከሃገሪቱ ህዝብ ወደ 85 % ይጠጋል የሚባለውን አርሶ አደር ግብርና መር በሚል የኢኮኖሚ ፖሊሲ አፍነው ይዘው፣ ከዚያ ውጭ ያለውን የአነስተኛ የኢንዱስትሪ መስክ ደግሞ በ EFFORT ተቆጣጥረው፣ የተረፈውን ደግሞ የልማት መንግስትን መቃወምን ወንጀል በማድረግ እያስፈራሩ በስልጣን ላይ ለዘለአለም ለመቆየት የሚያስችላቸው ዕቅድ አላቸው። በዚህ ላይ የደህንነትና የፖሊስ እንዲሁም የወታደሩ ክፍል እቅዳቸውን የሚቃወሙን ለማፈን በተጠንቀቅ ቆሞ ይገኛል።

እውነታው ይሄን ስለሚመስል ***ቤን*** በሚሰራው ዶኩሜንታሪ ከዚህ ቀጥሎ የሰፈሩትን ከተጨባጩ ሁኔታ የመነጩ ሃቆች እንዲያስብባቸው ከተቻለውም እንዳሉ እንዲያቀርባቸው እንጠቀዋለን። ህዝቡ ከእንቅልፍ ነቅቶ መራመድ ጀምሯል የሚባለው ቀልድ መሆኑን፣ ያለው መንግስት በእኛ አቆጣጠር በ 2002፣ 2007 እና 2012 በይስሙላ ምርጫዎች አሸናፊነት ሽፋንና የሃይል እርምጃዎች ስልጣን ላይ እንደሚቆይ፣ በዚህ ወቅት ሰላማዊም ሆነ የአመጽ "ተቃዋሚዎች" በከተማና በገጠር ከመሹለክለክ ያለፈ ፋይዳ ያለው የፓለቲካ ተጽዕኖ በመንግስት ላይ መፍጠር እንደማይችሉ፣ ከ 2012 በኋላ ህዝቡ በመንግስትና በተቃዋሚ ነን ባዩች ላይ ዕምነት በማጣት በግብታዊነት ከዳር እስከዳር በገገርው ፓርቲና በመንግስት ላይ እንደሚነሳ፣ በአመራር እጦት የህዝብ መነሳሳት በገጠር በሚሽሎክሎኩ ታጣቂ ሃይሎች እጅ እንደሚገባ፣ በወቅቱ ወደ አምስት የሚደርሱት ታጣቂ ሃይሎች ሃገሪቱን እንደሚከፋፈሏት፣ ብዙም ሳይቆይ ሃግሪቱን ወደ ስድስት ትንንሽ ሃገሮች ለዘለቄታው እንደሚለወጥዋትና የሚፈልጉትን ዓለም ዓቀፍ እውቅና እንደሚያገኙ፣ እነዚህ አዳዲስ ሃገሮች ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በታጣቂ ሃይሎች በጉልበት ከመገዛት በስተቀር የተሻለ ህይወት እንደማይገጥማቸው እንደሚገነዘቡ፣ አዲስ የስቃይ ኑሮም መግፋት እንደሚጀምሩ ማሳየት ማለት ነው።

ከላይ የተገለጹት አደጋዎች ሊቀንሱ ብሎም ሊወገዱ የሚችሉት በልማትና እድገት ብቻ ሳይሆን በፖለቲካው መስክ በሚደረግ መጠነ ሰፊ መሻሻል ነው። የገገርው ፓርቲና መንግስት ዲሞክራሲያዊ ምርጫን ተግባርዊ ካላደረጉ፣ በህገ መንግስቱና በሌሎች ህጎች የተረጋገጡ መብቶችን ካላከበሩ፣ የፍትህ ስርዓቱ በተለይም ፍርድ ቤቶችና የአቃብያነ ህግ

ታቋሞች ከገገርው ፓርቲና ከመንግስት ነጻ ካልሆኑ፤ በተቃዋሚዎችና በጋዜጠኞች ላይ የሚካሄደው ህገ ወጥ ድርጊት ካልቆመ፤ ታጣቂ የብሄርም ሆነ ህብረ ብሄር ድርጅቶች በሰላማዊ መንገድ በፖለቲካ የሚሳተፉበት መንገድ ካልተመቻቸ፤ ከጎርቤት ሃገሮችም የሰላም ግንኙነት ካልተፈጠረ ሃገራችን ከቻይና በፊት በአፍጢሟ መደፋቷ አይቀርም። ህዝቡም ሊያጋጥም የሚችለውን ሁኔታ በመገንዘብ ከወዲሁ ዝግጅት ቢጀምር በኋላ ከመደናበር ይድናል። ቢያንስ ስለሁኔታው ዛሬውኑ ውይይት መጀመር ይጠቅማል።

***ቤን*** መጪው ጊዜ ካለፈው የባሰ አደጋ እንደተጋረጠበት ማሳየት ካልቻለ የሚሰራው ዶኩሜንታሪ ከተራ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያነት እንደማያመልጥ ሊረዳ ይገባል።

## *3. 2. "... እየሰከነ፤ አካባቢውን እያወቀና እየተረጋጋ መራመድ የጀመረ ህዝብ"*

ከላይ በንዑስ ርዕስ የቀረበውን ለመዳሰስ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ በድጋሚ በመጥቀስ እንጀምር።

"በሁሉም አቅጣጫ - በልማቱም፤ በዲሞክራሲውም፤ እንዳልኩት ከእንቅልፉ የነቃ ሃገርና
ህዝብ ስለሆነ (ከረጅም እንቅልፍ በኋላ) በመጀመሪያ ሲነቃ እንደሚያጋጥመው ሁሉ
የተወሰነ የመደናበር ሁኔታ ቢኖር የሚገርም አይደለም።"

ልማት በግንባር ቀደምነት የመንግሥት ሥራ ነው። ህዝብ ታክስ በመክፈል የዜግነት ግዴታውን ከመወጣት አልፎ መንገድና ድልድይ የመስራት፤ ኤሌክትርክና ውሃ የማዳረስ፤ የስልክና ሌሎች የመገናኛ መስመሮች የመዘርጋት፤ የገንዘብና የዋስትና ድርጅቶች እንዲስፋፉ ህግ የማውጣትና አፈጻጸሙን የመከታተል ቀጥታኛ ሃላፊነት የለበትም። የግሉ የኢኮኖሚ ክፍል ደግሞ የግል ነው። የህዝብ አይደለም፤ ለህዝቡም ተጠሪ አይደልም። በልማት እጅግ አናሳ ድርሻ ቢኖረውም የመንግስትን ድርሻ መተካት አይጠበቅበትም። የልማቱ ስራ የመንግስት በመሆኑ ከተስማማን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህዝቡ ልማትን በሚመከት ተወራጨ፤ ተደናበረ የሚሉት በምን ምክንያት እንደሆነ ግልጽ አይደላም። እርግጥ እርሳቸው የሚመሩት መንግስት በልማት ላይ በመደናበሩ አገሪቱ አሁንም የአለም ጭራ ሆና ትገኛለች። ይሄን ሁኔታ የመለወጥ ድርሻ የእርሳቸው መሆኑን ካልተቀበሉና ህዝቡን በማይመለከተው ጉዳይ ደንባራ ብለው በባዶ ሜዳ የሚሰድቡት ከሆን "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" ይሆናል። ህዝብ የሚለውን የሚሰማ መንግስት ባለበት ሃገር በሚመርጣቸው ተውካዮቹ አማካይነት ልማትን ይከታተላል። ከህዝብ ፍላጎት ውጭ የሚሰራን መንግስት ያሰናብታል። በሃገራችን የዚህ አይነት መንግስት የለም።

ዲሞክራሲም ቢሆን በህገ መንግስቱና በሌሎች ህጎች በመረጋገጡ ህዝብ "ዲሞክራሲ በተግባር" ሲል መንግስት "አይቻልም" በማለቱ የሚፋለሙበት ጉዳይ እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚሉት ህዝብ መወራጨትና መደናበር የሚያሳይበት አይደለም። መወራጨትና መደናበር አሳይቶም ከሆነ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን ዲሞክረሲያዊ መብት ተጠቅሞ በነጻነት ልደራጅ፤ ልሰበሰብ፤ ልወያይ፤ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞ ላሰማ ሲል በተቃራኒው በመንግስት የሚደርስበትን ግድያ፤ እስራትና ስቃይ ለማስቀረት ከሚያደርገው ትግል የመጣ ነው። ለዲሞክራሲያዊ መብት መከበር የሚደረግ ትግል ደግሞ በማናቸውም መለኪያ መወራጨትና መደናበር በማለት ሊጣጣል አይችልም።

እንግዲህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የመንግስታቸውን መወራጨትና መደናበር የህዝብ መወራጨትና መደናበር አድርገው ከወሰዱት በህዝብና በመንግስት መሃል ያለውን ልዩነት

አልተረዱም ወይም አውቀው ሊይሳስቱን ይሞክራሉ ማለት ነው። ነገር ግን ሁለቱም አይሰራም። በእኛ እምነት "እየሰከን አካባቢውን እያወቀና እየተረጋጋ መራመድ የጀመረ ህዝብና ሃገር" የሚሉት በልማቱም በዲሞክራሲውም ለአስራ ስምንት ዓመታት መንግስት ሲወራጭና ሲደናበር እያየ "ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆን?" በማለት ሁኔታውን በቅርብ የሚከታተውለውን፣ ሲቻለው እየታገለ፣ ሞት፣ እስራትና ስቃይ ሲበዛበት ደግሞ ፊርቶ አንገቱን ደፍቶ ዝም የሚለውን ህዝብ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህዝቡን ኪሳቸው ውስጥ እንደከተቱትና በፈለጉ ጊዜ እንደሚያወጡት ዕቃ አድርገው ነው የቆጠሩት። ***ቤን*** ይህን ሁኔታ በሚሰራው ዶኩሜንታሪ ውስጥ በአደባባይ በመናገር ስህተት መሆኑን ማስረዳት ካልቻለ ምንም እንዳልሰራ ነው የሚቆጠረው። ህዝቡ አሁንም በልማትም በዲሞክራሲም ጉዳዩች ጥያቄዎች እንዳሉትና እነኛን ጥያቄዎች መመለስ ያለበት መንግስት መሆኑን ፣ ጥያቄዎቹ ካልተመለሱ ከላይ በቁጥር 3.1 የዘረዘርናቸው አደጋዎች አይቀሬነታቸውን ሊያስገነዝብ ይገባል ባዩች ነን። ባጭሩ ሀገሪቱ ባለችበት ሁኔታ ከአስር ዓመታት በላይ አትቆይም።

## 4. ***ፌደራሊዝም፣ የኢትዩጵያ አንድነት፣ የመከፋፈልና የመጥፋት አደጋ፣***

***ቤን*** ወደ ሌላ ጥያቄዎች ያልፋል። "እኛ ውጭ ያለነው ስለ ፌደራሊዝም አወቃቀር ያለን ሁኔታ ጥሩ አይደለም። ስለእውነት ከልቤ ኢትዩጵያን ይበታትናታል ብዮ እፈራለሁ። ሁሉም እኔ ትግሬ ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ ካለ ትልቁ ስዕል የኢትዩጵያ ነገሯ አትጠፉም፣ አትደበዝዝም ወይ የሚል ስጋት አለኝ። … እናንተስ አትፈሩም? In the long run ተለጥጦ ኢትዩጵያን ሊከፋፍላት፣ ሊያጠፋት፣ አንድነቷን ይሰብራል የሚል ፍራቻ አይመጣባችሁም? "በማለት ይጠይቃቸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለጥያቄዎቹ ዝግጁ መልስ ነበራቸው። ሚሊዩን ጊዜ ተጠይቀው የመለሷቸው ጥያቄዎች ስለሆኑ እነዚያን መልሶች እዚህ መድገም አፍታም አልወሰደባቸው። አዲስ ነገር ቢኖር መልሶቻቸው ረዘም ያሉና ግልጽ መሆናቸው ብቻ ነው።

ለዚህ ጥያቄ የሰጧቸው መልሶች በሁለት የተከፈሉ ሆነው በመጀመሪያው ክፍል "የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ" የሚል አገላልጽ ይጠቀማሉ። ቀጥለውም የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ የሚኖረው ኢትዩጵያዊ መሆን እንደክብር እንደጸጋ እያንዳንዱ ዜጋ የሚወስድበት የራሱ በቂ ምክንያት ሲኖረው እንደሆነ ያስረዳሉ። በሁለተኛው ክፍል አንድነት ካስፈለገ በሃገሪቱ ህዝቦች መካከል አለ የሚሏቸውን ልይነቶች መቀበል አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ።

እዚህ ላይ በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ። እርግጥ በሃገራችን "የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ" አለወይ? መልሱ "አጠራጣሪ ነው" ነው። በአሁን ወቅት "የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ" አለ ቢባል እንኳ መኖሩም ሆነ ጥንካሬው በምን ይረጋገጣል? መልሱ "በምንም አይረጋገጥም" ነው። አሁን ኢትዩጵያ በምትባለው ሃገር ውስጥ ካሉት ህዝቦች ውስጥ ተገንጥለው የራሳቸውን መንግስትና ሃገር መመስረት የሚፈልጉ እንደሌሉ ምን ማረጋገጫ አለ? መልሱ "ማረጋገጫ የለም" ነው። አነሰም በዛ የሃያ እና የሰላሳ አመታት የመገንጠል የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ሁለት ሶስት የብሄር እንቅስቃሴዎች ባሉበት ሃገር እንዴት በእርግጠኛነት "የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ" አለ ለማለት ይቻላል? መልሱ "አይቻልም" ነው። የመገንጠል መብትን በህገ መንግስቱ ውስጥ አስፍሮ የመብቱን በህጉ ውስጥ መኖር የሚቃወሙትን ሁሉ በጠላትነት የሚያይ መንግስት ባለበት ሃገር የዚያ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር "አይዟችሁ፣ አንበታተንም" ቢሉ ይታመናሉ? መልሱ "አይታመኑም" ነው። ኤርትራ እንድትገነጠል በጦር በዲፕሎማሲና በፕሮፓጋንዳ ያገዙ፣ ከተገነጠለችም በኋላ በመንግስትነት ተሽቀዳድመው እውቅና የሰጡ፣ የዚህ ድርጊታቸውን ትክክልኛነት ሸንጣቸውን ገትረው የተከራከሩ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመሩት ህዝብ መበታተንን እንዴት አይፈራም? መልሱ

"ቢፈራ አይወቀስም" ነው። በህገ መንግስት የተረጋገጡ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች በአደባባይ በሚጣሱበት ሃገር ዜጎች ኢትዮጵያዊ መሆንን እንዴት እንደክብርና እንደጸጋ ይወሰዳሉ ተብሎ ይጠበቃል? መልሱ "ሊጠበቅ አይገባም" ነው። ዋነኛ የመበታተን አደጋ ምክንያት የነዚህ መብቶች መጣስ አይደለምን? መልሱ "ነው" ነው። በዚህ ሁኔታ ሃገሪቱ ለመበታተን የተጋለጠች ነች? መልሱ "በትክክል የተጋለጠች ናት" ነው። የኢትዮጵያዊነት ፍይዳ ደካማ ቢሆንም ተጠግኖ ሊድን ይችላል? መልሱ "ይችላል" ነው።

በማያጠራጥር ሁኔታ በአሁን ወቅት የኢትዮጵያዊነት ፋይዳ ደካማ ነው። ድክመቱን ለማረምና ወደ ጥንካሬ ለመለወጥ የሚቻለው እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ምንም ነገር አደረግን አላደረግን ለውጥ አያመጣም" በማለት እጃችንን አጣጥፈን በመቀመጥ ሳይሆን በቅድሚያ የመበታተን አድጋ መኖሩን አምኖ መቀበልና አድጋውን ለመቀነስ በመጨረሻም ለማስወገድ የሚረዱ እርምጃዎችን በመውሰድ ብቻ ነው። የኢትዮጵያዊነት ፋይዳ "ስለፈለግን" ብቻ አይመጣም። እንዲመጣ ጠንክሮ መስራት ይገባል። ለዚህ ደግሞ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ ትልም (deliberate nation building project) ያስፈልጋል። አሁን ሃገሪቱ የዚህ አይነት ፕሮጀክት የላትም። እኛ ሊኖራት ይገባል ባዩች ነን። ፕሮጀክቱ ትክክለኛ ፌደራሊዝምን በስራ ከማዋል አንስቶ - ህገ መንግስቱን፤ ዲሞክራሲንና ሰብአዊ መብቶችን መሉ ለሙሉ እስከማክበር እንዲሁም ቀድሞ በነበሩ መንግስታት በደል የደረሰባቸውን ብሄሮችንና ህዝቦችን ይቅርታ እስከመጠየቅ ድረስ ሊሄድ ይችላል። በነገራችን ላይ በሃገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅሬታ ያላቸውን ብሄሮችንና ህዝቦችን ይቅርታ የመጠየቅ ፍንጭ ያሳዩት አሁን በእስር ላይ የሚገኙት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ናቸው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዚህ ጅምር ቢገፉበት ብዙ የፖለቲካ ካፒታል ያገኙበት ይሆናል።

እዚህ ላይ አንድ አሳሳቢ ነገር ማንሳት ያስፈልጋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለ በቂ ምክንያትና ማስረጃ የመበታተን አደጋ አልፏል ብለው ስላመኑ በአንድ ወቅት ሲሞክሩት የነበርውን ብረት ካነሱ የብሄር ድርጅቶች ጋር የመወያየት ጉዳይ እርግፍ አድርገው ትተው በሃይል መደምሰስ ላይ አትኩረዋል። ይሄ መቼም እልም ያለ ስህተት ነው። ሊደመስሷቸው እንደማይችሉና ሙከራውም ገንቢ አለመሆኑን ተረድተው ድርጅቶቹ በሰላም ፖለቲካ እንዲሳተፉ ሁኔታ መፍጠርና መድረኩንም ማስፋት ይገባቸዋል። የድርጅቶቹ ዓላማ ያለውን መንግስት አሸንፈው የራሳቸው መንግስት ማቆም ቢሆንም ቶሎ ስላልተሳካ መሳሪያቸውን አስቀምጠው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ ማለት አይደላም። በቅርቡ እንደታየው የተወሰኑ እጅ ስለሰጡ ሁሉም በተመሳሳይ እጅ ይሰጣሉ ማለትም አይደላም። ለሃያና ሰላሳ ዓመታት በበረሃ እንደቆዩ ወደፊትም ሲያመቻቸው አደጋ እየጣሉ፤ ሲጠቁ እያፈገፈጉ እዚያው በረሃ የሚቆዩ ይኖራሉ። ሁኔታው አመቺ ሆኖ ሲያገኙት (ለምሳሌ በ 2012 አካባቢ ሊከሰት ይችላል ያልነው ዓይነት የህዝብ መነሳሳት ሲኖር) በአጋጣሚው ይጠቀማሉ። ከላይ እንደተባለው የእነዚህ የብሄር ድርጅቶች የመዳከም ዜና በሰፊው ቢናፈስም የቀሩትን ለመደምሰስ ከመሞከር ይልቅ በሰላም ፖለትካ እንዲሳተፉ ማድረግ በረጅም ጊዜ ለብሄሮች የተሻለ መግባባትና መቀራረብ ያግዛል። አሁን ህብረ ብሄር ነን ባይ ድርጅቶች እየተቀላቀሏቸው የግጭቶቹን ወረዳዎች እያሰፉ መምጣታቸውንም መዘንጋትም አይገባም። እንደሚሰማው ከሆነ የኋለኞቹ  ከፊተኞቹ ይበልጥ አደገኞች ሳይሆን አይቀሩም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠንካራ በሚመስሉበትም ወቅት የሰላም ፍለጋ ፖለቲካ ካላራመዱ ሀገሪቱን ሌላ ከፍተኛ መዘዝ ውስጥ እንደሚከቱና ከመዘዙ ሊያወጧት እንደማይፈልጉ ግልጽ ይሆናል። ምናልባትም ይሄ በሃገሪቱ ላይ እስካሁን ካደርሷቸው ጉዳቶች የላቀውን ቦታ እንደሚይዝ አያጠራጥርም። ***ቤን*** ሰውየው የ nation building project እንዲኖራቸው ማሳሰብ ካልቻለ ዶኩሜንታሪው አንዳችም አድናቂ እንደማያገኝ ከወዲሁ ግልጽ ሊሆንላት ይገባል እንላለን።

### *4. 1 ኢትዩጵያዊነትና የጠቅላይ ሚኒስትሩ “የመንደር ነፋስ” ብሂል፤*

ይሂ የሚገርም ነጥብ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እኛ ከምንለው በተቃራኒው “ኢትዩጵያዊነት … የመንደር ነፋስ የሚያፈናቅልውና የሚያፈራርሰው አይደለም። (ኢትዩጵያዊነት ለመኖሩ) ምክንያት አለው። ተፈላጊ የሚሆንበትና ጥንካራ የሚሆንበት ምክንያት አለው። ስሜት አይደልም። ነባራዊ ሁኔታ ነው”ይላሉ። ባጭሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዩጵያዊነት ፍይዳ በአስተማማኝ ሁኔታ አለ ባይ ናቸው። አባባላቸውን ለመደገፍ የሚያቀርቡት ማስረጃ ግን አሳማኝ አይደልም። እርሳቸው በቀጥታ አነጋገርም ባይሆን በመንደር ነፋስነት የሚመስሏቸው የሃገሪቱን አንድነት የሚፈታተኑት የመገንጠል አቋም የሚያራምዱ የብሄር ንቅናቄዎችን ነው። ያልተገነዘቡት ነገር የተወሰነም ቢሆን ንቅናቄዎቹ የሚያካሁዱት የሽምቅ ጦርነትና ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ከላይ ከገላጽናቸው ችግሮች ጋር ተዳምረው ሃገሪቱ ከመንደር ነፋስ ያንሰ ሃይል ሊያፈራረሳት በሚችልበት ሁኔታ አመቻችተዋት መገኘቷን ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ መኖር ብቻ ሳይሆን ጠንካራ መሆኑን ሳያቅማሙ ይናገራሉ።

> “በእኔ እምነት ግን የኢትዩጵያ ፋይዳ በጣም ጥልቅ ነው። በጣም መሰረታዊ ነው። ትልቅ መሰረታዊ ምክንያቶች አሉት። 80 ሚሊዩን ህዝብ አንድ ላይ ስናጫበጭብ ይበልጥ እንደመጣለን። ጠንካራ ተወዳዳሪ እንሆናለን። ተመጋጋቢ ኢኮኖሚ ነው ያለን። በፖለቲካውም መስክ እንደዚሁ። የህገራችንን አንድነት በማስጠበቅም እንደዚሁ። ከትምህርት አኳያ ስንሄድ ተነጣጥለን የምናገኘው የቴክኖሎጂ አቅምና አንድ ላይ ተሰባስበን የምናገኘው የቴክኖሎጂ አቅም የተላያየ ነው የሚሆነው። ስለዚህ መሰባሰቡ የራሱ ጠንካራ ምክንያት አለው።”

አሁን ማን ይሙት የኢትዮጵያ ህዝብ ኢትዩጵያዊነትን ፋይዳ ብሎ የያዘው ወይም የተሰባሰበው በአለም ደረጃ ተደማጭነት ለማግኘት ወይም ጠንካራ ተወዳዳሪ ለመሆን አስቦ ነው? በኢኮኖሚውስ ቢሆን ማንና ማን ናችው ተመጋጋቢ ኢኮኖሚ ኖሯቸው በኢኮኖሚው ምክንያት “ጥልቅ” - “መሰረታዊ” የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ ወይም ስብስብ የገነቡት? ቢያንስ ፖለቲካው እዚህ እንዴት እንደገባ አይታወቅም። በፖለቲካም ጥልቅ የኢትዮጵያዊነት ፋይዳ አለ ነው የሚሉት? ይህ ፋይዳ ምን አይነት ፋይዳ ነው? አንድነት የማስጠበቁም ሁኔታ እንኳ ፋይዳ ነው ቢሉ አድማጭ አያጡም። በዚህ ጉዳይ ህዝቡ ብዙ ጊዜ መንግስትን ስለተጋፈጠ ትኩረት ሰጥተው ሊናገሩበት የሚገባ ጉዳይ ነበረ። የቴክኖሎጂው ጉዳይ እንዲያው ያለቦታው የገባ ስልሆነ ቢረሱት ይሻላል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዘረዘሯቸው የኢትዩጵያዊነት ፋይዳ ወይም የህዝቡ መሰባሰብ ምክንያቶች እንደምክንያት ሊወሰዱ ቀርቶ ለጉዳዩ ጭራሽ አግባብ የላቸውም። ከላይ እንደተባለው ሃገሪቱን ከመበታተን ለማዳን ፍላጎት ካላቸው እቅድ አውጥተው፤ ፕሮጀክት ነድፈው በፖለቲካውም፤ በፍትህም፤ በኢኮኖሚውም፤ በመልካም አስተዳደርም፤ በባህልም መቀራረብ ሊፈጥሩና ሊያዳብሩ የሚችሉ ሰፊ ጥረቶች ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ባለው ሁኔታ የሚቀጥሉ ከሆነ ግን አለ የሚሉት የኢትዩጵያዊነት ፍይዳም ሆነ መሰባሰብ እንጥፍጣፊ በቅርቡ ጥሏቸው ይነጉዳል።

### *4. 2. ኢትዩጵያዊነትና የጠቅላይ ሚኒስትሩ “በአሸዋ ላይ የተገናባ አንድነት” ብሂል፤*

*በኢትዮጵያውያን መካካል ልዩነቶች መኖራቸው እርግጥ ነው። ልዩነቶች የሉም ብሎ አጥብቆ የሚከራከር እዚህ ግባ የሚባል የህብረተስብ ክፍል በሌለበት ሃገር ልዩነቶችን እያጋነኑ ማውራት*
*የኢትዮጵያዊነት ፋይዳን ለመገንባት ብዙም አይጠቅምም። ልዩነቶች* nation building vision *በሌላቸው ሰዎች እጅ ሃገር ለማፍረስ ዋነኛ መሳሪያቸው ነው። በሃገራችን የምናይውም ሂደት ይሄ ነው።*

*ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያውያን መካከል ያሉትን ልዩነቶች ሲያጋንኑ እድሜንና ጾታን ሳይቀር ይጨምሩበታል። በሃገራችን የሃይማኖት ልዩነቶች ቢኖሩም አልፎ አልፎ በቅርቡ የተከሰቱ ግጭቶችና አለመግባባቶች ይሄን ያህል ግዙፍ አይደሉም። ዋናው ችግር የብሄሮች ነው። እርሳቸው ሃይማኖትን፣ ብሄር ብሄረሰብን፣ ጾታን፣ እድሜን፣ እንደልዩነቶች ከዘረዘሩ በኋላ ልዩነቶቹን ልናከብር* (celebrate) *ልናደርግና ልናስተናግድ ይገባል ይላሉ። እስኪ ራሳቸው የተናገሩት እናንብ፣*

> *"በሀይማኖት የተለያየን ነን። በብሄር ብሄረሰብ የተለያየን ነን። በጾታ፣ በእድሜ የተለያየን ነን። ኢትዮጵያዊነታችን ይሄን ማስተናገድ የማይችል ከሆነ፣ ይሄን የማያከብር* (celebrate) *የማያደርግ ከሆነ የጥንካሬው ምንጭ ይደርቃል። ልዩነታችን የጥንካሬያችን ምንጭ እንዲሆን ከተፈለገ ግን ይህን ልዩነት ለማስተናገድ፣ ለማቀፍ መቻል አለብን"*

***ቤን*** *የጠቅላይ ሚኒስትሩን መልስ ከሰማ በኋላም ስጋቱ አልቀነሰም። ሃይማኖትን፣ ጾታን፣ እንድሜን ጨማምረው እንደችግር ሲያመጡለት ምን ያድርግ? "ግን ሊለጠጥ አይችልም ወይ?" በማለት ይጠይቅና የራሱን ሁኔታ እንደምሳሌ ያቀርባል። "እኔ ለምሳሌ ኦሮሞ ነኝ። አባቴ ኦሮሞ ነው። ኦሮሞ* more emphasis *እየተሰጠው በመጣ ቁጥር ኢትዮጵያዊነት አይደበዝዝም ወይ? " ይላቸዋል። በሙሉ ልብ ስጋቱን ለማጥፋት ጥያቄውን እንደሚከተለው ይመልሳሉ።*

> *"አይደበዝዝም። ምክንያቱም የእርስዎ ኦሮሞነት ብቻ እርስዎን አይገልጽዎትም። ኦሮሞ ኬንያዎች አሉ። እርስዎ ኦሮሞ ኬንያዊ አይደሉም። ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ኖት። ስለዚህ በኢትዮያዊነት ወይም በኦሮሞነት ብቻ አይገለጹም። አንዱ ከሁለቱ ተነጥሎ አይታይም። እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ ነው እየሰፋን የመጣው። … በጣም ጥሩ ኦሮሞ ሆኖ በጣም ጥሩ ኢትዮጵያዊ መሆን ይቻላል። አንዱ ከሌላው ውጭ ሊመጣ አይችልም። በተግባር እየታየ ያለውም ይሄ ነው።"*

*እኛ እንደሚገባን የኦሮሞ ብሄርተኞች* (nationalists) *ስለኦሮሞ ህዝብ እንጂ ስለኬንያዊነት ወይም ኢትዮጵያዊነት አያወሩም። በደፈናው የኦሮሞ ህዝብ "የራሱን እድል በርሱ የመወሰን" መብቱን ተግባርዊ ማድረግ መከልከል የለበትም ነው የሚሉት። ማናቸውም ዲሞክራሲያዊ መንግስት ይህን ማገድ ስለማይችል አንድነት የፈልገ መንግስት ተስፋውን የሚጥለው በዚያው በኦሮሞው ህዝብ ላይ ነው። ትቼህ አልሄድም፣ አብሬህ እቆያልሁ እንዲልው ማለት ነው። ከዚያ ውጭ ኢትዮጵያዊ ወይም ኬንያዊ ካልሆንክ የራስህ ሃገር አይኖርህም ሊባል አይችልም። እዚህ ላይ የኤርትራን ገጠመኝ ማስታወስ ይረዳል። ለመበታተን አደጋ መፍትሄው ልዩነቶች መኖራቸውን መቀበል ብቻ ሳይሆን ለብሄር - ብሄረሰብ ጥያቄዎች ኢትዮጵያዊነትን በሚያጎለብት መልኩ አጠቃልይ የፓለቲካ መፍትሄ መፈልግ ነው። በጥንቃቄ ከታየ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ ግምት* (guess) *ላይ የተመሰረተ ነው። ኦሮሞነት ከኢትዮጵያዊነት ውጭ አይገልጽም የሚል አስተሳሰብ እየሰፋን*

በተግባርም እየታየ ነው ላሉትም ከግምት ሌላ ምን ማስረጃ እንዳልቸው አናውቅም። ቢያንስ ኦሮሞዎችን በሚመለከት ማለታችን ነው።፡

በመቀጠልም የብሄር ጥያቄ አደባባይ መውጣቱ ህብረተሰቡ እንዳሰከነው በእርግጠኛነት ይናገራሉ። ሰከነ ሲሉ ምን ማልታቸው እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም ይሂኛው አባባላችውም ቢሆን እንደሌሎቹ ግምት ከመሆን አያልፍም። ግን እርግጠኛንታቸውን ያስተውኋል።

“ከዚህ በፊት የኦሮሞ ጥያቄ በፍጹም እንዳይነሳ፣ ምክንያቱም ሃገሪቱን ይበትናል ይባል በነበረ ጊዜ ውስጥ ውስጡን የመነጣጠል ስሜትና መንፈስ በከፍተኛ መጠን ያደገበት ሁኔታ ነበረ። ደርግ በወደቀ እለት የነበረው የመነጣጠል ስሜት በኦሮሚያም ሆነ በሌላው የሃገሪቱ አካባቢ እና አሁን ያለው ስሜት በጣም የተለያየ ነው። አሁን ህብረተሰቡ ሰክኗል። ኦሮሞነቱን ለማረጋገጥ ኢትዩጵያዊነቱን ማቋረጥ እንደማያስፈልገው በተጨባጭ አይቷል። ይልቁንም ኦሮሞነቱን በትክክል ለመግለጽ ኢትዩጵያዊነቱን መደረብ እንዳለበት፣ ከዚህ ውጭ ሊታሰብ እንደማይገባ ተገንዝቧል። ሌላውም ብሄረሰብ እንደዚሁ።”
ሁታው ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚሉት ቢሆን በማን እድል? የኦሮሞ ህዝብም ሆነ ሌላው “የሰከነው” ያለውን መንግስት የጭካኔ እርምጃ ፓለቲካ ፈርቶ ላለመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን ማስረጃ አላቸው? የሃገሪቱ እስር ቤቶች በኦሮሞና በሌሎች ብሄርተኞች እንደተሞሉ በሚነገርበት ሃገር ብሄር ብሄረሰቦች ማንነታቸውን ለማረጋገጥ ኢትዩጵያዊነታቸውን ማቋረጥ አይፈልጉም ለማለት ይቻላልን? ሰውየው ብሄር ብሄረሰቦች ማንነታቸውን ለመግልጽ ኢትይጵያዊነትን መደረብ እንዳለባቸው ታዟል፣ ከዚህ ውጭ ቢያስቡ ይቀጣሉ ቢሉ ይሻል ነበር። የሃገሪቱ ሁኔታ የሚያሳየው ያንን ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልሳቸውን እንደሚከተለው ይደመድማሉ።

> *“ስለዚህ ተለጥጦ ሄዶ ሃገሪቱን ሊበታትን ይችላል የሚለው ስጋት በእኔ እምነት የሃገርቱ አንድነት በአሸዋ ላይ የተገነባ አድርጎ የመውሰድ ስጋት ነው። በፊት በአሸዋ ላይ ተገንብቶ ሊሆን ይችላል። አሁን በአሸዋ ላይ የተገንባ አይደልም። በጋራ ጥቅም ላይ ነው።”*

በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አንድነት የሚባለውም ራሱን በቻለ ጥያቄ ምልክት የሚታለፍ ነጥብ ነው። አንዳንድ ብሄሮች ሌሎች በእኛ የተፈጥሮ ሃብትና ሰፊ የሰው ሃይል ያለአግባብ ይጠቀማሉ በማለት ይወቅሳሉ። ክዚህም የተነሳ በሃገሪቱ ያለውን የብሄሮች ግንኙነት በበዝባዥና ተበዝባዥበት ይፈርጁና በሃብቻችን ላይ ሙሉ ቁጥጥር ማጣትም ሆነ ማግኘት የራሳችንን ዕድል በራሳችን ከመወሰን ጋር የተያያዘ ነው ይላሉ። በተለይ ስልጣን ላይ ሙጭጭ የሚል አናሳ ብሄር ከ resource access ፍላጎት ሌላ አጀንዳ ሊኖረው እንደማይችል አጽናኦት አድርገው ይናገራሉ። እስከተውሰነ ደረጃ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ ይሄን ነጥብ መሸፋፈን የሚሞክር ይመስላል። ሰውየው እንደሚሉት በልዩነት ላይ የተመሰረተ አንድነት የሚፈልጉ ከሆነ የጋራ ጥቅም የሚለውን ተረት ተረት ወደጎን አድርገው ሁሉን አቀፍ ሰፊ እቅድ አውጥተው በዚያ አቅጣጫ ተግተው መስራት ይጠበቅባቸዋል። አሌ ካሉ ተራ የማግባባት ንግግር ትተው የሃገሪቱን በቅርቡ መበታተን “በደስታ” ቢጠብቁ ይሻላል።

***ቤን*** በዚህ ጉዳይ ምን ይል ይሆን? የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር እንደወረደ ሊያስጎነጨን ከሞከረ መቼም አይንህ ላፈር ነው የምንለው። የተሻለ ነገር ለማየት በጉጉት እንጠብቃለን።

### *5. የምግብ እጥረት (food shortage) እንጂ ረሃብ (famine) በሃገሪቱ የለም፣*

*ቤን* “አንድ ነገር አለ፤ ጠባሳ ጥሎ ያልፈ አሁንም ያለ” በማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ወደ ረሃብ ጉዳይ ይወስዳቸዋል። በመቀጠልም “ለፓርላማ ያቀረቡትን ሪፖርት ተከታትያለሁ። ብዙ ስራዎች ተሰርተው የረሃብ ነገር - መንግስት ይደብቃል የሚባል ነገር - በ default የሚነገር ነው። እውነት የሚደበቅ ነገር አለወይ? በምግብ ራስን የመቻል ጉዳይ ላይ ብዙ ሰርተናል ወይ? ለምንደነው 6 — 7 ሚሊዩን ተራበብን የምንለው? እንደመሰረተ ልማቱ አልተሄደበትም ማለት ነው?” ይላቸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልሳቸውን የሚጀምሩት የ 1977 ን የህዝብ ብዛት ከ 2002 የህዝብ ብዛት ጋር እናወዳድር በሚል ነው። በመቀጠልም በ 25 አመታት የህዝብ ብዛት በ 36 ሚሊዩን እንጻደገ፤ ከ 6 — 7 ሚሊዩን ህዝብ ተራብ የሚባለውም ይህን ተጨማሪ ህዝብ መመገብ ተችሎ እንደሆነ፤ እንዲያውም በአስራ ስምንቱ የእርሳቸው አስተዳደር ዓመታት ወቅት የምግብ እጥረት (food shortage) እንጂ ረሃብ (famine) እንጻልነበረ ዘረዘሩ። የህዝብ ቁጥር ወደ 76 — 77 ሚሊዩን ማደጉ እውነት ቢሆንም እንደ እርሳቸው አባባል ከዚህ ቁጥር ላይ ተራብ የሚባለው 6 እና 7 ሚሊዩን ህዝብ ሲቀነስ 70 ሚሊዩን የሚሆነው ይመገባል። ለአስራ ስምንት ዓመታትም አልተራበም።

> “...ባልፉት አስራ ስምንት ዓመታት ረሃብ ታይቶ አይታወቅም። የምግብ እጥረት ያጋጥማል። በየዓመቱ ግን የውጭ እርዳታ ተጨምሮበት የራሳችንም ርብርብ ተጨምሮበት
> በየዓመቱ በሺሆች ቀርቶ በመቶዎች፤ በአስሮች ሰው በማይሞትበት መልኩ እየተቋቋምው
> ቆየተናል። አሁንም እንቋቋመዋለን።...”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምግብ እጥረትና በረሃብ መካከል ያለውን ልዩነት የሚገልጹት የሞተ ሰው መኖር አለማኖሩን እንደመለኪያ በመውሰድ ነው። ሰው ካልሞተ የምግብ እጥረት እንጂ ረሃብ የለም ይላሉ። ረሃብ ቢኖርም የሚገኘውን ምግብ ሞትን በሚያስወግድ ሁኔታ በጥቂት በጥቂቱ በማከፋፈል የህዝብን እድሜ ማርዘም እንደሚቻል በሚገባ ያውቃሉ። በዚህ ሁኔታ በሃገራችን የተዘረጋው አሰራር የምግብ እጥረትን የሚፈታ ሳይሆን ረሃብን የተሻለ መልክ የሚያሲዝ famine management system ነው ቢሉ ምንኛ በተሻለ ነበር። ይህ ደግሞ በቋሚነት የምግብ እርዳታ የሚፈልግ ህዝብ መፍጠር የቻለ አስቀያሚ አሰራር መሆኑን መካድ አይቻልም።

በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በምግብ እጥረትና በረሃብ መካከል ልዩነት ቢኖርም እንደኛ ባለው ሃገር በተግባር ያላቸው ልዩነት የደበዘዘ ነው። ሞት እንደመለኪያ ከተወሰደ የምግብ እጥረት አንድ፤ ሁለት ወይም አምስት ዓመት ተጨማሪ እድሜ ሰጥቶ የሚገድል ሲሆን ረሃብ ግን ወዲያው ጊዜ ሳይሰጥ የሚገድል ነው። የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የምግብ እጥረት ገዳይነቱ አጠያያቂ አይደለም። የተራብ ህዝብ በቀላሉ በበሽታ ስለሚጠቃ እድሜው አጭር ነው። በቀን አንድ ጊዜ በልቶ ሞትን ማዘግየት የቻለ ህዝብ ስላልሞተ ብቻ የምግብ እጥረት እንጂ ረሃብ የለብህም ሊባል አይችልም። በቅርብ ለምናውቀው ሰዎች የምግብ እጥረት ያለበት ህዝብ 6 — 7 ሚሊዩን ብቻ አይደለም። በትንሹ ከ 70 — 80 % የሚሆነው የሃገሪቱ ህዝብ በዚህ ሊሸፈን ይችላል ባይ ነን። ግዙፍ መረጃ ካስፈለገ በመንግስት በጀት የሚተዳደረውንና መንግስትን በምግብ ጉዳይ የማማከር ብሄርዊ ሃላፊነት የተጣለበትን የምግብ ጥናት ድርጅት ባለሙያዎች ማንጋገር ይበቃል። እዚህ ላይ አሳሳቢው ነገር የቃላት ምርጫ ሳይሆን ከረሃብ ጋር ሲወዳደር የምግብ እጥረት እንደ አነስተኛ ችግር አልፎ ተርፎም ከረሃብ ጋር ሲወዳደር እንደ ጥሩ ውጤት ተደርጎ መቅረቡ ነው። ለምሳሌ የግብርና እድገት አለ ተብሎ ተጋንኖ የሚነገረው የምግብ እጥረት እንጂ ረሃብ የለም የሚለውን ክርክር ለመደገፍ ነው። ይሂ መቸም ተደግሞ መነገር አይገባውም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ “በ 1977 ረሃብ ነበረ። በ 1965  - 1966 ረሃብ ነበረ። ሁለቱም ጊዜ ተደብቋል” ይላሉ። መንግስታቸው በቅርቡ ረሃብ ደብቋል በመባል በመከሰሱ ሁኔታውን ለማስተባበል ብዙ እንደደከሙ ይታወቃል። በመጨረሻ ያገኙት ማስተባበያ ያው የምግብ እጥረት እንጂ ረሃብ የለም የሚለውን ነው። አሁን አሁን ባለስልጣኖቻቸውና ረዳቶቻቸው ሁሉ የሚናገሩት አንድ ቋንቋ ሆኗል። የምግብ እጥረት እንጂ ረሃብ የለም የሚል። የምግብ እጥረትም ሆነ ረሃብ ችግሩን ደብቀው እንደነበርና የተደበቀው በመውጣቱ መንግስታቸው ሁኔታው መኖሩን ለማመን እንደተገደደ እናስታውሳለን። ደግነቱ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ረሃብም ይበሉት የምግብ እጥረት ችግሩን ማሸነፍ እንዳልቻሉ ያምናሉ። ድክመታቸውንም “... 5 — 6 — 7 ሚሊዮን ህዝብ መመገብ አለመቻላችን እንደስኬት ሳይሆን እንደጉድላት እናይዋልን። ተጨማሪ ሥራ እንደሚያስፈለገን ያሳያል፡፤ ገና work in progress ነው” በማለትይገልጹታል።

ለሰውየው ከአስራ ስምንት ዓመታት የሙከራ ጊዜም በኋላ የምግብ እጥረትን ማስወገድ work in progress ነው። መንግስታቸው ስልጣን ላይ በቆየባቸው ዓመታት በሙሉ የሚታወቅበት ነገር ቢኖር አንዳንድ በጥንቃቄ የተመረጡ፤ ነገር ግን ጥቅም የሚያስገኙ ድክመቶን በአደባባይ ማመን ነው። መንግስታቸው ብልጠት በተሞላበት ሁኔታ ድክመትን አምኖ ከሄደቱ ጥቅምን መፈብረክ የሚችል ኩባንያ መሆኑን በሙሉ ልብ መናገር ይቻላል። በተለይ የምግብ እጥረትንና ረሃብን በሚመልከት በማያጠራጥር ሁኔታ ብልጠቱ ሰርቷል። የምግብ እጥረት አለብን ሲባሉ የውጭ መንግስታትና ድርጅቶች ምግብ ይለግሳሉ፤ ገንዘብም ይሰጣሉ። ረሃብ ተባለ የምግብ እጥረት እውነታውን ስለሚያውቁ ከመንግስት ጋር አይከራከሩም። ችግሩ ግን በየዓመቱ ያው “ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ” መሆኑ ነው። ። ምግብ አጠረው የሚባለው ህዝብ ቁጥር ብዙም የማይለወጥ stabilize ያደረገ በየዓመቱ ወቅቱን ጠብቆ ብቅ የሚል ዕዳ ሆኗል። የሚከሰትበት አካባቢም ከሞላ ጎደል ይታወቃል። ምናልባት የአስቸኳይ ገዜ አዋጅ አውጆ ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሄ መስጠት ከዚህ ብሄራዊ ውርደት ይገላግለን ይሆን? አሁንማ ብሄራዊ እፍረት መሆኑ ቀርቶ ሃገር ውስጥም ሆነ ውጭ ዜናው በምስል እያታገዘ ሲቀርብ የሚሰቀጥጠው ሰው እየጠፋ መጥቷል። ፈረንጆቹ ሳይቀሩ የተለመደ ዓመታዊ ድብርት ይሉታል።

አንድ በውል የሚታወቅበት ነገር ቢኖር ለረሃብም ሆነ ለምግብ እጥረት መፍትሄው ከረሃብ ወደ ምግብ እጥረት መሄድ አይደለም። ከላይ እንደተገለጸው ልዩነታቸው እስከዚህም ደረት አያስነፋም። በግብርና ምርት ራስን መቻልም በቂ አይደለም። መፍትሄው ተረፈ ምርት surplus ማምረት ብቻ ነው። ችግሩ ግን surplus ማምረት አይፈለግም ይሆናል። ሃገሪቱ ውስጥ ያለው “ኢንዱስትሪ” እርሻን፤ አገልግሎትን (ሆቴሎችንና መጓጓዣን)፤ ግንባታን፤ ማኑፋክቸሪን፤ ማዕድንና ንግድን የያዘ ሲሆን ሰራተኛ የመቅጠር አቅሙ አሁንም እጅግ ዝቅተኛ ነው። ግብርናው surplus ማምረት ከቻለ ጉልበታቸው ለእርሻ ሥራ የማያስፈልግ ገበሬዎች በሌላው የኢንዱስትሪው መስክ እንዲቀጠሩ ሁኔታ ይፈጥራል። እንደሁኔታው ከእርሻ የሚላቀቁት ሰዎች በሚሊዩኖች ይቆጠሩ ይሆናል። ሰዎቹ ሥራ ካላገኙ ከፍተኛ ቀውስ ቢከተልስ የሚል ፍራቻ ስልጣን በጣም አድርገው በሚወዱት ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ድርጅታቸውና መንግስታቸው ዘንድ በመኖሩ አርሶ አደሩን በመሬት ላይ አስረው ማቆየት ይመርጣሉ። የሚፈራው ቀውስ መፍትሄ አልባ ስላይደለ surplus ማምረት ቀውስ ሊያስከትል ይችላል በሚል ፍራቻ ረሃብን ወደ ምግብ እጥረት በማውረድ ወይም በምግብ ራስን መቻል ፖሊሲ ወስኖ ማቆየት አይገባም። ህንድና ቻይና በእርሻ ሰብል surplus ከማምረታቸው በፊት የጎላ የኢኮኖሚ እድገት አለማሳየታቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። መንግስት የሚፈራው ቀውስ ስላላጋጣማቸው ከግብርና የተላቀቀውን በብዙ ሚሊዩን የሚቆጠር ህዝብ የት እንዳደረሱት መጠየቅ አይከፋም። በተለይ ቻይና ኢንተርኔት ማፈን፤ ኢ. ሜልና ሽቦ አልባ ስልኮችን መሰለል ማሳየት ብቻ ሳይሆን አርሶ አደሮች ወደ ከተማ

እንዲፈልሱ በመፍቀድ ረሃብን እንዴት መቀነስና በመጨረሻም ማስወገድ እንደቻለች እንዲሁም ኢኮኖሚዋን ለማሳደግ እንዴት እንደተጠቀመችባቸው ያላትን ልምድ ማካፈል አለባት።

*ቤን* ምን ያህል በጠቅላይ ሚኒስትሩ መልስ እንደረካ ወይም እንዳዘነ ማወቅ የምንችላው የሚሰራውን ዶኩሜንታሪውን ስናይ ብቻ ነው። ስለሆነም በትዕግስት እንጠብቃለን።

*6. በፊትም መሬትን ለማልማት የግል ባለሃብቶች ቢግቡ የሚል እምነት ነበረን፤*

**ቤን** ለውጭ ኢንቬስትሮች በመሰጠት ላይ ያሉት የእርሻ መሬቶችን በሚመለከት "ለምሳሌ በቅርቡ የሣኡዲ ኢንቬስትሮች እንደመጡ (ተነግሯል)። እዚህ አገር ትልቅ የኢንቬስተር እጥረት አለ። አሁን እየመጡ ነው። በ agriculture አካባቢ. ለምሳሌ ቴክኖሎጂውን ያሳድግልን ይሆን? ጥቅሙ ምን ያህል ነው? ገበሬውን አፈናቅሎ ለባለሃብት የሚሰጥ ተደርጎ ይታያል። አስተያየትዎ ምንድነው?"
በማለት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ይጠቃቸዋል።

እርሳቸውም መንግስታቸውና ድርጅታቸው ይወቀሱ የነበሩት ኢንቬስተር አይፈልጉም፤ በአርሶአደሩ ላይ ተንጠልጥለው ሃገሪቱን ከልማት ወደኋላ አስቀሩ እየተባሉ እንደነበረ አስታውሰው ያኔም ቢሆን የአርሶ አደሩን ምርታማነት ማሳደግ ለምግብ ዋስትና አስፈላጊነት አቋማቸው እንደነበረ ተናገሩ። በመቀጠልም "የአርሶ አደሩን ማሳና ምርት ወደ ጎን ብሎ የሚካሄድ የግል ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ማህበራዊ ቀውስ ያመጣ እንደሆነ እንጂ ልማት አይመጣም። የአርሶ አደሩን ጥረት በሚደግፍና (ጥረቱን በማይነካ መልኩ) ግን የግል ኢንቨስትመንት መስፋፋት አለበት" አሉ።

*ቤን* ስለቴክኖሎጂ ያነሳው ጥያቄ ጥሩ ነው። መልሱ በሰፋፊ እርሻዎች ጥቅም ላይ የሚውለው ቴክኖሎጂ ለአርሶ አድሩ አግባብነት የለውም፤ የሚያስክትለውም እድገት የለም ነበረ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግን ምናቸው ሞኝ ነው ጥያቄውን በዝምታ ያልፉና የተቀናቃኞቻቸውን ወቀሳ ስህተትና የእርሳቸውን ትክክለኛነት በመተንተን ጊዜ ያጠፋሉ። ለአስራ አምስት ዓመታት "ግብርና መር ኢኮኖሚ" የድርጅታቸውና የመንግስታቸው ፖሊሲ እንደነበር ቢታወቅም አሁን ያን ፖሊሲ እንዳላራመዱ በመምሰል "ለምግብ ዋስትና አስፈላጊነት" ብቻ ይጠቀሙበት እንደነበረ ሊያሳምኑ ይቃጣቸዋል። በ 20 ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ "ግብርና መር ኢኮኖሚ" እና የአርሶ አደሩ "ርዕዩተ ዓለም" በምግብ እንኳ ራስ አለማስቻላቸውን የሃገራችን ልምድ በበቂ ሁኔታ ያሳያል። "ግብርና መር ኢኮኖሚን" እና የአርሶ አደሩ "ርዕዩተ ዓለም" ን ጥያቄ ላይ ማስቀመጥ የአርሶ አደሩን ማሳና ምርት ወደጎን ማለት ወይም ማህበራዊ ቀውስ መናፈቅ አይደለም። ይህ ግብርናንና አርሶ አደሩን የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ማዕከል የማድረግ አቋም አንዳንዶች እንደሚጠረጥሩት ለፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ የቀረበ ከመሆኑ በስተቀር በተግባር የተሞከረ አይደለም። ተሞክሮም ቢሆን አልተሳካም።

*ቤን* ሌላ ጥሩ ጥያቄ ያነሳል። የጥያቄው መሰረተ ሃሳብ አሁን ኢንቬስተሮች እየገቡበት ያለው የእርሻ መስክ ጥቅሙ ምን ያህል ነው የሚል ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄውን ወዲያው አይመልሱም። ወደመጨረሻ ገደማ ለሌላ ጥያቄ በሰጡት መልስ "የሰራተኛ ጉልበት ይከፍላል። ምርት በማሳደግ ኤክስፖርት ያጠናክራል" አሉ። መልሱ ትክክል ቢሆንም ችግር አለው። በመጀመርያ መንግስት ሃገሪቱ ያላትን ብቸኛ ስትርተጂክ ሪሶርስ - መሬትን - ለውጭ ካፒታል አሳልፎ በገፍ ሲያቀርብ ብሎም በኪራይ ሲሰጥ ከተቻለ ህዝብ ራሱ፤ ካልተቻልም ተወካዩቹ አውቀውትና ተወያይተውበት በመጨረሻም ሲስማሙበት መሆን ነበረበት። ይህ ለይስሙላ እንኳ አልተደረገም። አዲስ ሙከራ እንደመሆኑ መጠን

ምን እንደሚያስከትል በግልጽ አይታወቅም። ህዝብ በቀጥታም ሆነ በተወካዩቹ አማካይነት በኪራይ የመስጠት ሂደቱን መከታተል፣ መቆጣጠርና መምራት በማይችልበት ሃገር፣ እርሻው ሊያስከትል የሚችለውን የአካባቢ ጤና ችግር ለመከላከል እውቀትም፣ አቅምም፣ ተቋሞችም በተጓደሉበት ሃገር፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ የህዝብ ቅሬታዎችን በገለልተኛነት ማስተናገድ የሚችሉ የፍትህ ተቋማት በተለም ነጻ ፍርድ ቤቶች በሌሉበት ሃገር መሬትን ለውጭ ካፒታል በገፍ መክፈት ጠቀሜታው አጠያያቂ ነው። ባለው ሁኔታ መንግስት ለህዝብ ተጠሪነት ስለሌለበት፣ ቢኖርበትም ተግባራዊ ስለማያደርገው በኪራይ ስለሚሰጣቸው መሬቶች በዜና ከሚገልጻቸው በስተቀር ሙሉ ዝርዝራቸውን አያሳውቅም። ስምምነቶቹንም ማየት አይቻልም። መንግስት እንደለመደው ይደብቃል ማለት ይቻላል። የኪራይ ስምምነቶቹም ቢሆኑ የሚደረጉት በአንድ በኩል ድሃና ገንዝብ ፈላጊ በሆነው መንግስት እና በሌላ በኩል ደግሞ ገንዘብና ስልጣን ባላቸው ሰዎች (ለምሳሌ ልዑልና የቀድሞ የሃገር ፕሬዚዳንት የነበሩና የእነርሱ መሰሎች) እና ጠንካራ ድንበር ዘለል ዓለም ዓቀፍ ኩባንያዎች መካከል ነው። ቅድመ ስምምነት ድርድሮቹም ሆኑ ስምምነቶቹ ራሳቸው በሃይል ሚዛን መዛባት ምክንያት ለኢንቬስተሮቹ ያደሉ እንደሆኑ በሰፊው ይነገራል። በመሬት ኪራይ አስተዳደር ጉዳይ መንግስት በእጅጉ የሚጎድለው የቴክኒክ እውቀትና ልምድ ድርድሮቹን ለመምራትም ሆነ ስምምነቶቹ በሚፈልገው አይነት ለማዘጋጀት አለመቻሉ ችግሮቹን እንዳባባሱ፣ አልፎ ተርፎም እጅግ አንስተኛ ገቢ እንዲሰበስብ እንዳስገደዱት የሚናገሩ አሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚሉት ሳይሆን በመካሄድ ላይ ያለው የግል እርሻ ኢንቬስትመንት የአርሶ አደሩን ጥረት አይደግፍም። የአርሶ አደሩን ጥረት በማይነካ መልኩ መስፋፋትም አይችልም። እውነት እንናገር ከተባለ የግል እርሻ ኢንቬስትመንት የአርሶ አደሩ ተፎካካሪ ስልሆነ ጥረቱን እንዲደግፍ ሊጠየቅ አይገባም፣ የመደግፍ ግዴታም የለበትም። ለነገሩ የግል እርሻ ኢንቬስትመንት ተግባራዊ ሲሆን አርሶ አደሮች ከዓለም ዓቀፍ ካፒታል ጋር ፉክክር እንዲገጥሙ መደረጋቸው ነው። ኢንቬስተሮች ይዘው የሚመጡት ካፒታል ብቻ ሳይሆን ኢንቬስት ስላደረጉ ለተወሰኑ አመታት ግብር ያለመክፈል፣ ውጭ ሃገር በሚልኩትም ምርት ላይ ቀረጥ ያለመክፈል፣ ከሃገር ውስጥ ባንኮች የገንዘብ ብድር የማግኘት ወዘተ መብት ይጠበቅላቸዋል። አርሶ አደሮች ግን ተመሳሳይ ድጋፍ አያገኙም። አልፎ ተርፎም ኢንቬስተሮችም ለገበያ ሊያቀርቡ የሚፈልጓቸው ምርቶች አርሶ አደሮች የሚያመርቷቸውና በሃገር ውስጥ ነጋዴዎች አማካይነት ለዓለም ዓቀፍ ገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶች ናቸው። ለምሳሌ ቻይናውያን ሃገራችን ውስጥ አምርተው ሃገራቸው መውሰድ የሚፈልጉት ሰሊጥ ከሃገራችን ይገዙት የነበረውን በሙሉ ያስቀራል። ህንድና ሌሎቹም ሃገሮች እንደዚሁ። ይሄ አርሶ አደሩ ለሃገር ውስጥ ገበያ ብቻ የሚፈለጉ ምርቶች እንዲያመርት ሊያስገድደው ቢችልም የዓመት ገቢው ይቀንሳል። በሰፊ መሬት ላይ፣ በርካሽ ጉልበትና የተሻሻለ ግብዓተ ምርት የተመረተ ምርት ርካሽ ስለሚሆን ወደ ውጭ የሚላከውም ሆነ ሃገር ውስጥ የሚሸጠው የአርሶ አደሩ ምርት ዋጋ ይወርዳል። የአርሶ አደሩ ገቢ ሲቀንስ ኑሮው ከአሁኑ ይብሳል፣ በቀላሉ ሊገላገልው በማይችለው ድህነትም ውስጥ ይወድቃል። ከተሜው የዚህ ሁኔታ ተጠቃሚ ቢመስልም በድህነት አርሶ አድሩን ይከተላል። የኢቬስተሮች ምርት ውጭ ሃገር ስለሚሸጥ ገበሬውን አይነካም ቢባል እንኳ በየአመቱ በብዙ ሚሊዩን የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችና ከተሜዎች እየተራቡ (በምግብ እጥረት እያተሰቃዩ) ሃገር ውስጥ የሚመረትን እህል የተሻለ የመግዛት አቅም ላላቸው የውጭ ኗሪዎች በርካሽ ዋጋ እንዲሸጥ ማደረግ አወዛጋቢ ጉዳይ ይሆናል። ውሎ አድሮም ማህበራዊ ቀውስ ማስከተሉ አይቀርም። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛው ኢንቬስተር ከውጭ የመጣ እንደመሆኑ ትርፉን የሚልከው ወይም የሚያስቀረው እዚያው ሃገሩ ነው። ይህ የሚፈጥረው የተበዝባዥነትን ስሜት ለሚፈራው የቀውስ እሳት ቤንዚን እንደማቅረብ ሊቆጠር ይችላል።

በዚህ እንግዳ የዓለም ዓቀፍ ካፒታል የእርሻ መሬት ወረራ አነሰም በዛ ተጠቃሚው ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ነው። እንደሚታየው ከሆነ ትንሽም ብትሆን ገንዘብ ከተሰጠው ሥራው ያገኘውን ነገር ሁሉ መቸብቸብ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚሉት መሬቶቹ የክልል መንግስታት (ለምሳሌ የቢኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የጋምቤላ) ሲሆኑ በሰጡት ውክልና መሰረት ኢንቬስትመንቱን የሚያስተዳድርላቸው የፌደራል መንግስት ነው። ገቢውን ማን እንደሚወስደው ግን የገለጹት ነገር የለም። በየክልሎቹ አርሶ አደሮችን ለመደጎም፣ መንገድ ለመስራት፣ የውሃ የመብራትና የስልክ መስመሮች ለመዘርጋት፣ ትምህርት ቤትና ክሊኒክ ለመክፈት፣ ወዘተ. የሚውል ከሆነ የካፒታል ወረራ የሚያስከትለው ጉዳት በገቢው ሊካካስ ይችል ችሆናል። የፌደራል መንግስት አፍኖ የሚያስቀረው፣ በሙስና የሚባክንና ለጭቆና ተቋማት በጀት የሚውል ከሆነ ጉዳቱ ግዙፍ ይሆናል። ይህ ደግሞ በየክልሎቹ ላሉ ታጣቂ የብሄርና ህበረ ብሄር ነን ባይ ድርጅቶች ቅስቀሳና ወታደራዊ እርምጃ ጥሩ ዒላማ እንደሚሆንና ለሃገሪቱ በቅርቡ መበታተን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ መካድ አይቻልም።

*ይህን ሁሉ አደጋ እያየ **ቤን** ምን ይል ይሆን? የመንግስትን ፕሮፓጋንዳ የሚደግም ከሆነ መሳቂያ መሆኑ ነው። ግን ያንን መንገድ የሚወስድ አይመስለንም።*

### *7. በመጪው ምርጫ የ 1997ቱ "ብጥብጥ" ይደገማል የሚል ስጋት የለም፣*

***ቤን*** ወደ ሌላ ጥያቄ ያልፋል። ይሄኛው ጥያቄው ስለመጪው ምርጫ ቢሆንም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ድርጅት እንደሚያሸንፍ በመተማመን እንዳልፈው የህዝብ ተቃውሞ ቢያጋጥማቸው እንዴት እንደሚያኮላሹት እንዲነግሩት ነበር። ጥያቄውን "ከፊታችን አንድ ምርጫ አለ።:ምርጫ በመጣ ቁጥር ፈሪ ሆኛልሁ። 1997 በመጥፎ አለቀብን" በማለት ይጀምርና "አንዳንዶች ምርጫ ያስፈልጋል ወይ እስከማለት ደርሰዋል" ይላቸዋል። ፈሪ የሆነበትን ምክንያት፣ 1997 ለምን በመጥፎ እንዳለቀበት እና አንዳንዶች ምርጫን የመጠራጠራቸውን ሁኔታ ሳያብራራላቸው በዝምታ ያልፈዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም አይጠይቁትም። ደግነቱ ሁለቱም ምክንያቶቹን ቢያውቁም በአደባባይ የሚነጋገሩባቸው ጉዳይች ስላልሆኑ ገሸሽ አድርገው ያልፏቸዋል።

የ***ቤን*** ጥያቄ ቀጥተኛ ነው።፡ "አሁን ከ 1997 በኋላ እንደ መንግስት ምን የተማራችሁት ነገር አለ? ኢህአዴግ ደግሞ ምን ተማረ? ለምሳሌ ይሄ engagement politics የምትሉት አይነት…" ይላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተራቸው እንደሚከተለው ይመልሳሉ።

> "በ 1997 ምርጫ የብዙ ክስተቶች ውጤት ነው። እንደመንግስት እንደ ድርጅት የነበሩብን ደካማ ጎኖች ነበሩ። በነዚህ ደካማ ጎኖች ተጠቅመው ጉዳት ለማድረስ የተዘጋጁ የውስጥም የውጭም ሃይሎች ነበሩ። ልምዱ - የዚህ ዓይነት ብጥብጥ ከምርጫ ጋር በተያያዘ ያልነበረው ሃገር፣ መንግስትና ህዝብ ነበረ። እንደ ጅርጅት እንደ ኢህአዴግ ያን ጊዜ በከተማ አካባቢ ትርጉም ያለው ህብረተሰቡን የማንቀሳቀስ ስራ ሰርተናል ለማለት አልችልም። መጀመሪያ የገጠሩን ህዝብ እናንቀሳቅስና ከዚያ ወደ ከተማ እንመለሳለን የሚል አቋም ነበረን። ገጠሩንም በተሟላ መልኩ ያላንቀሳቀስንበት ደረጃ ላይ ነበርን።"

ይህ መልስ ብዙ ጉዳዮችን ያነሳል። እንደተለመደው በቅድሚያ ድክመት ነበረብን በማለት ይጀምሩና ድክመቶችን ሲዘረዝሩ የልምድ ማጣትን በመጀመሪያ ይጠቅሳሉ። ልምድ የሚሉት በምርጫ ወቅት የተከሰተውን "ብጥብጥ" መደምሰስ ከሆን ያለብዙ ችግር አመራሩን በእጃቸው አስገብተው አከናውነውታል። "ብጥብጥ" የመደምሰስ ልምድ አልነበራቸውም በማለት ሀገርንና ህዝብን ከመንግስታቸው ጋር አዳብለው ማቅረባቸው ለምን ይሆን? ሀገር መቼም ግዑዝ ስለሆነ በዚህ አይታማም። ህዝብ ደግሞ ከእርሳቸው በተቃራኒው አልያም በፍርሃት በርቀት ቆሞ እያለ "ብጥብጥ" የመደምሰስ ልምድ አልነበርውም ማለት ራሱን እንዲደመስስ እንደመጠየቅ ይቆጠራል። "ብጥብጡ" በመንግስታቸውና እርሳቸውን በሚቃወሙ ከህዝቡ በወጡ ሰዎች መካካል የነበረና በእርሳቸው የጭካኔ እርምጃ የተደመሰሰ ነው። በዚህ ሁኔታ ሃገርንና ህዝብን ከመንግስታቸው ጋር አምታተው ማቅረባቸው ህዝቡ ከእኔ ጋር ነበር ለማለት ይመስላል። ግን አንዳንዴ ትዝብትን መፍራት ጥሩ ነው፤ በባህላችንም ምን ይሉኛል የሚባል ነገር አለ። እርሳቸው አልሰማህ አሉት እንጂ ህዝቡማ መንግስትዎ በቃኝ ብሏቸው ነበር። በቃኝ ማለቱን እንዳመኑ ከላይ ከቀርበው ንግግራቸው መረዳት ይቻላል። በከተማም በገጠርም ህዝቡን አላንቀሳቀስንም ማለት ምን ማለት ነው? እኛ እንደሚገባን አልፈለገንም ማለት ነው።

የፈረደበት ***ቤን*** ጥልቅ ይልና የስትራተጂ ጉዳይ ያነሳል። "በአብዛኛው በካድሬዎች ትመኩ ነበር ይባላል። የሚነግሯችሁን ነበር የምትሰሙት የሚሉ አሉ። ከህዝቡ ጋር እንቅስቃሴ የጀመሩት (one to one) ከዚያ በኋላ ነው ይባላል። ያኔ ካድሬዎችን ያምኗቸው ነበር ማለት ነው?" ጠቅላይ ሚኒስትሩ "አንዱ ጉድለት እርሱ ነው" በማለት ይቀጥሉና ቀደም ብለው የተናገሩትን እየተንበዛበዙ መድገም ይጀምራሉ። ከ 1997 ምርጫ ወዲህ በልማቱ ጥሩ ውጤት እንዳገኙ፤ ህዝቡም "ተስፋ፤ ብርሃን" እንዳየና ከሁኔታው "ከፍተኛ ትምህርት" እንደወሰደ፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም የእንደዚያ ያለ አካሄድን ጉዳት ተገንዝበው ከጉዳት ለመቆጠብ የሚሞክሩ እንዳሉ፤ ከውጭ የነበረውንም ጣልቃ ገብነት በሂደት እንደተገነዘቡትና ችግሩ አሁን እንደሌለ አስረዱ። በመጨረሻም የ 1997 ሁኔታ ይደገማል የሚል ምንም ስጋት እንደሌላቸው በርግጠኛነት ተናገሩ።

በእርግጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከ 1997 ምርጫ ውጤት ብዙ ተምረዋል። ስልጣናቸውን ለማጣት ምንም ባልቀራቸው ሰዓት ሃይል ተጠቅመው የህዝቡን ድል ቀልብሰዋል። ዋና ያገኙት ትምህርት ሰፊ ቅድመ ዝግጅት ካደረጉ ስልጣን ላይ ለመቆየት ተመሳሳይ የቅልበሳ መንገድ መጠቀም እንደማያስፈልጋቸው ነው። ስለሆንም ያለፉትን አምስት ዓመታት የመንግስትን፤ የድርጅታቸውን፤ የግለሰቦችን ወዘተ. resources በመጠቅም የድርጅታቸውን አባላትን ቁጥር ሲያበዙ፤ ተቃዋሚዎችን ሲከፋፍሉና ሲያዳክሙ ቆይተው አሁን በልበ ሙሉነት የሚያሸንፈኝ የለም ወደማለት ተሸጋግረዋል። መጪውን ምርጫ ተከታትለው እንዳይዘግቡ ነጻ የግል ጋዜጦችንና ጋዜጠኞችን፤ በምርጫ ወቅት በታዛቢነት እንዳይሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፤ ጥፋት ቢፈጸም እንዳይወቅሱ ዲፕሎማቶችንና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችን ደረጃ በደረጃ ከመጪው ምርጫ ሂደት ገሸሽ አድርገዋል። ህዝቡ በመጪው ምርጫ ድምጽ ቢሰጣቸው "ተስፋ - ብርሃን" ስላየና ትምህርት ስላወሰደ ሳይሆን ያለፈውን ምርጫ ውጤት በሀይል መቀልበስ በሀዘን በማስታወስና እንዳይደገም በመፍራት ነው የሚሆነው። ሃሰት ካሉ እስኪ መንግስታቸው ለዓመታት ሲያካሄደው የቆየውን የህዝብን፤ የጋዜጠኞችን፤ የድርጅቶችን፤ የዲፕሎማቶችንና የተቃዎሚዎችን ወከባ ለመጪው ሦስት ወራት በማቆም ለነጻ ምርጫ ሁኔታዎችን ያመቻችና የ 1997 ውጤት እንደማይደገም ይመልከተው። በራሱ ከተማመነ ይሞክረው፤ እንደማያደርገው ግን እናውቃለን።

ባለው ሁኔታ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግስት መጪውን ምርጫ "ቢያሻንፍ" ባይደንቅም ሂደቱ የሚፈጥረው ቅሬታ ሃገሪቱን ይበልጥ እንደሚከፋፍል እንዲያውም መንግስታቸውን

በትጥቅ ለሚፈታተኑ የብሄርና የህብረ ብሄር ድርጅቶች ነን ባዩች መጎልበት እንደሚያግዝ፣ ወደሚፈልጉትም ሀገራቱን የመበታተን ግብ ገፍቶ እንደሚያደርሳቸው አያጠራጥርም።

***ቤን*** *በዚህ ነጥብ ላይ ምን እንደሚል መስማት እንናፍቃለን።*

***8. አመጽና የጉልበት ሥራ ያስፈልጋል የሚሉ ራሳቸው በስፍራው ተገኝተው ይሞክሩት፣***

***ቤን*** *ዳያስፖራውን አልረሳውም። " 1997 ላይ ተወደደም ተጠላም እኛ ዳያስፖራዎች ብዙ influence ነበረን። አሁን መጪውን ምርጫ በተመለከተ ለዳያስፖራው ሊያስተላልፉ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?" ይላቸዋል።*

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በ 1997 ምርጫ ወቅት መንግስታቸውና ድርጅታቸው ዳያስፖራውን በሚመለከት የነበረውን ድክመት እንደሚከተለው ይገልጻሉ። "የሃገር ቤቱን (የገጠሩንና የከተማውን) ካስተካከልን በኋላ ዳያስፖራውን engage አድርገን ልናስተካክለው እንችላለን የሚል አስተሳሰብ ነበረን"። በመቀጠልም "... ዳያስፖራውን engage ለማድረግ የተወሰኑ ሙከራዎች ተደርገዋል። አሁንም አጥጋቢ ስራ ተሰርቷል ብዮ አልወስድም" አሉ። "ማስተካከል" ከሚለው ቃል አጠቃቀማቸው የምንረዳው ዳያስፖራው "መስመር ስቷል" የሚል እምነት እንዳላቸው ነው። ይህን በተናገሩ በወሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው የለም ዳያስፖራው ከኛ ጋር ነው በሚል ጠቅላይ ሚኒስትሩን የሚቃረን ንግግር አደረጉ። በምን ስሌት እንደሆን ባይታወቅም 19 000 የዳያስፖራ ሰዎች 17 ቢሊዩን ብር ኢንቬስት አድርገዋል፣ ለ 80 000 ዜጎች ሥራ ከፍትዋል በማልት ቁጥሩን አኻጎደጎዱት። ትንሽ ቀደም ሲል ብሔራዊ ባንክ በዚህ ዓመት ከውጭ ወደ ሃገር የተላከው ገንዘብ መጠን ቀነሷል ሲል መደመጡ ይታወሳል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ "እያንዳንዱ ውጭ ያለ ኢትዩጵያዊ በአካል ሊሳተፍበት የማይፈልገው ነገር ሌላ ሰው እንዲሰራልት ማበረታታት የለበትም።... ለምሳሌ ድንጋይ መወርወር የማይፈልግ በውጭ የሚኖር ኢትዩጵያዊ ራሱ እዚህ አዲስ አበባ መጥቶ መወርወር የማይፈልግ አዲስ አበባ ያለው ድንጋይ እንዲወረውር ገንዘብ ማዋጣት፣ ማደፋፈር የለበትም። ምክንያቱም *በገንዘቡ የሰው ህይወት እየገዛ ነው ማለት ነው። ይሄ ደግሞ ከሰብዕና ጋር አይሄድም።* የተቸገረ ህዝብ፣ ብዙ እውቀት የሌለው ህዝብ በገንዘብና በእውቀት በመጠቀም በእኔ ላይ እንዲደርስ የማልፈልገውን እኔ ልሰራ ያልፈልግሁትን እንዲሰራ መድረግ *በአጠቃላይ ነውር ይመስላኛል።... ከሞራልም አኳያ አጠያያቂ ነው ለሚል እምነት አለኝ"* በማለት በፊት የተናገሩትን አጠናከሩ።

እዚህ ላይ በገንዘብ የሰው ህይወት የመግዛትን ነገር ምን አመጣው ትሉ ይሆናል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይናገሩ የነበሩት ድንጋይ ስለመወርወር ስለሆነ ድንጋይ መወርወር ህይወትን ሊያሳጣ እንደሚችል በግልጽ ማመናቸው ነው። በ 1997 ምርጫ ወቅት መሸነፋቸው በእርሳቸው፣ በመንግስታቸውና በድርጅታቸው ላይ የፈጠረው መደናገጥና ትእግስት ማጣት፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች ስልጣን ለመረከብ ዝግጁ አለመሆን፣ የምርጫ ቦርድ ውጤትን አፍኖ መይዝና ማዘግየት እንዲሁም በሁኔታው ቅር የተሰኙ ሰዎችን የሚያረጋጋ በመጥፋቱ ችግሩ አደባባይ ወጥቶ ብዙ ድንጋይ ወርዋሪዎች ህይዋታቸውን አጡ። ግድያው ወንጀል ቢሆንም እስከአሁን ድረስ መቀጣት ይቅርና የተከሰሰም ሰው ስለሌለ ጠቅላይ ሚኒስትሩም፣ መንግስታቸውም፣ ድርጅታቸውም፣ ግላሰቦችም ከዚህ ሁኔታ አልተማሩም። አህንም ሰውየው ድንጋይ ወርዋሪዎች ለህይወታችሁ ተጠንቀቁ ማለታቸው ነው።

ሌላው ነገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ውጭ የሚኖር ኢትዩጵያዊ አገር ውስጥ ያለውን ድንጋይ እንዲወረውር ገንዘብ ማዋጣትና ማደፋፈር የሰው ህይወት መግዛት ሰለሆነ ከሰብእና ጋር

የማይሄድ ነውር፤ ከሞራልም አኳያ አጠያያቂ ያደርጉታል። እርሳቸው ራሳቸው ከሰብእና ጋር የማይሄድ ነውር፤ ከሞራል አኳያም አጠያያቂ ያሉት ድርጊት እንደ ወንጀል ተቆጥሮ በቅርቡ ሰዎች በሌሉበት በሞትና በእድሜ ልክ እስራት ሲቀጡ፤ ንብረታቸውንም ሲያጡ አይተናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ገንዘብ ተዋጣለት፤ ተገፋፋ ፤ ችግረኛ፤ ብዙ እውቀት የሌለው ያሉትም ወንጀል ሊፈጽም ዝግጅት ሲያደርግ ደርሼ አከሸፍኩበት ብለው በሞትና በእድሜ ልክ እስራት ቀጥተውታል። የገንዘብ ጉርሻና ድጎማ እንዲሁም የማደፋፈር ቅስቀሳ ሰለባ ለመሆኑ የማያጠራጥርን የግላሰቦች ስብስብ ድርጊት "ከሰብእና፤ ከነውርና ከሞራል" ጥያቄነት አልፎ ያለርህራሄ በሞትና በእድሜ ልክ መቅጣት "በአንድ ራስ ሁላት ምላስ" የሚያስኝ የፍርደ ገምድል ተግባር ነው። በቀልንና ቂጭትን እንጂ ፖለቲካዊ አመዛዛኝነትንና ሆደ ሰፊነትን አያሳይም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመጨረሻ "የአመጽም የጉልበትም ስራ ብዙ ርቀት የሚወስድ እንዳልሆነ መገንዘብ የሚጠቅም ይመስለኛል" ካሉ በኋላ "በፊት አመጽና ብጥብጥ ያስፈልጋል የሚል አቋም የነበራቸው ሰዎች - በፊት በደርግ ጊዜ - ራሳቸው ሊያደርጉ የማይፈልጉትን ነገር ሌላ ሰው እንዲያደርግ የሚጠይቁ አልነበሩም። አሁንም ብጥብጥና አመጽ ያስፈልጋል የሚሉ ካሉ በሌላ ሰው ደም - በሌላ ሰው ላብ በነርሱ ገንዘብ ብቻ እንዲከናወን መፈለጋቸው ትክክል አይደላም" በማለት መልሳቸውን ይደማድማሉ። ወንዶች ከሆናችሁ ወደ ቆላው ወረድ በሉና ሞክሩን ማለታቸው ነው። ይሄን ያሉት ሰዎቹ እንደማይሞክሩት ስለሚያውቁ ነው።

እኛ ሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ተቀምጠው " በለው … በለው …" የሚሉትን አንደግፍም። ገነዘብ አዋጣም አላዋጣ "በለው" ካለ በሰላማዊ ትግልና በሰላማዊ የስልጣን ቅብብሎሽ የማያምን፤ የሃገሪቱ ህልውና ደንታ የማይሰጠው በተቃራኒው ህልውናዋን ለአደጋ የሚያጋልጥ ሃይል ነው። ትናንት እንዳልነው ዛሬም ይህን ሃይል ወደ ሰላምዊው ትግል ተመለስ ካልሆነልህ እረፍ እንለዋለን። በዚህ ጉዳይ ***ቤን*** ከእኛ ጋር ነው ብላን እናስባልን።

9. ***እነርሱ ብር አላቸው፤ እኔ የለኝም።***

***ቤን*** አሁን ወደ መጨረሻው ጥያቄ አለፈ። ጥያቄው ላይ ላዩን ሲያዩት ብስለት የጎደለው፤ በቋንቋ የተኻኀረኀረና ያልተቋጨ ይመስላል። ይዘቱ ግን ጥሩ ነው። ጥያቄው ፦ " As a prime minister, life comfortable ይመስላኛል። ለምሳሌ መንገድ ላይ ትራፊክ አይዞትም። እንደበረሩ ነው የሚሄዱት። We should admit — it is comfortable. እንደው ከዚህ ሲወጡ አቶ መለስ ዜናዊ ሆኖ ለመኖር psychologically ተዘጋጅተዋል? ምቾቱም ይጠፋል" የሚል አስተያየት የተቀላቀለበት ነበረ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈጠን ብላው "እንዳመለካከቱ ነው። እንደምቾትም ማየት ይቻላል። እንደ እስር ቤትም ማየት ይቻላል" በማለት ጀምረው ይህንኑ ሃሳብ አስፋፍተው ከገለጹ በኋላ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሥራ ለቀው ከአዲሱ ሁኔታ ጋር ራሳቸውን ማስተካከል ያቅተኛል የሚል ግምት እንደሌላቸው ተናገሩ። የሚኖሩት ሃገር ውስጥ እንደሆን፤ በዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ስለመስራት ወዳጆቼ ያሏቸው ሰዎች ሃሳብ ያቀረቡላቸው ቢሆንም ያንን እንደማያደርጉ፤ እረፍት ምን እንደሆነ ማየት እንደሚፈልጉና እንደሚናፍቃቸው፤ በጊዜ ማጣት ያላነበቧቸውን ማንባብ ያልጻፏቸውን መጻፍ እንደሚፈልጉ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሃገር ውስጥ ለመኖር መወሰናቸው ከምን እንደመነጨ በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም። እርሳቸውም ምክንያቱን አልገለጹም። ቤንም ለማወቅ አልፈለገም። እኛ ስለፈሩ ነው የሚል ግምት አለን። በጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በድርጅታቸውና በመንግስታቸው ውሳኔ ሃገራችን የዓለም ዓቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ስምምነት

አላጸደቀችም። ከዚህም የተነሳ ራሳቸውና የሚመሩት መንግስት ባለስልጣኖች ፈጽመዋቸዋል በተባሉት የጦር ወንጀሎች፣ በሰብአዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎችና ጀኖሳይድ በፍርድ ቤቱ ዓቃቤ ህግ አልተከሰሱም። እንዚህ ወንጀሎች ለመፈጸማቸው በርካታ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችና መንግስታት ዘገበዋል፣ ማስረጃዎቹም በእጃቸው አሉ። እዚህ ላይ በአኝዋክ፣ በኦጋዴን፣ በኦሮሚያ፣ በሶማሊያ፣ በአዋሳ፣ ከ 1997 በፊት በአዲስ አበባና በአካባቢዋ እንድሁም ከ 1997 ምርጫ ውጤት ጋር በተያያዙ የተፈጸሙ የፖለቲካ ግድያዎችን፣ የአካል ማጉደል ድርጊቶች፣ እስራቶች፣ ቶርቸር፣ ስደት እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ሃገራችን የዓለም ዓቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት ስምምነት ባልማጽደቅዋ ፍርድ ቤቱ ክሶቹን አይቶ መወሰን ባይችልም ብዙ መንግስታት በሃገራቸው ባላቸው ህግ መሰረት ይህን ማድረግ ይችላሉ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንዴ ስልጣን ከለቀቁ በዓልም ዓቀፍ ህግ መሰረት አሁን ያላቸው ያለመከሰስ መብት ስለሚነሳ ስልጣን ላይ በነበሩ ወቅት ለፈጸሙት ወንጀል ወንጀሉን ለመቅጣት ህግ ባላቸው ማናቸውም ሃገር ሊከሰሱ ይችላሉ። ስልጣን ላይ አለመሆናቸው ሂደቱን ቀላል ከማደረጉ በስተቀር ዛሬም ቢሆን ክሱ ሊጀመር ይችላል። ክሱ ማናቸውም ከላይ የተዘርዘሩት ወንጀሎች ወይም ሌሎች መሰል ወንጀሎች ተፈጽመውብኛል ወይም በቤተሰቤ ላይ ተፈጽሟል የሚል ግለሰብ ወይም ሌላ ይመለከተኛል የሚል አካል ሊያቀርበው የሚችል ሲሆን ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት አስገዳጅ ፍርድ ሊሰጥ፣ ከዚያም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብቻ ሳይሆኑ የመንግስታቸውና የድርጅታቸው አመራር አባላት በተገኙበት ሊያዙና ፍርዱ ሊፈጻምባቸው ይችላል። ሰውየው ከፊታቸው የተደቀነውን አደጋ ስለሚያውቁ "እዚችው ሞታለሁ እንጂ ከሃገር አልወጣም" የሚሉት ያለምክንያት አይደለም። ውሳኔያቸው ምናልባት የሚፈልጉትን ደህንነት ይሰጣቸው ይሆናል። ተከሰሰም አልተከሰሰ አንድ ከላይ የዘረዘርናቸው ዓይነት ወንጀል ፈጽሟል የተባለ ሰው በዓለም ዓቀፍ ተቋማት ውስጥ ቀጣሪ ያገኛል ለማለትም ያስቸግራል። እርሳቸውን፣ መንግስታቸውንና ድርጅታቸውን የሚቃወም በርካታ ህዝብ ከሃገር ውጭ መኖሩን እያወቁ እግራቸውን ካነሱ ጨርቃቸውን ጥላው አብደዋል ማለት ነው።
ውጭ ሃገር መቀጠርና መኖር ቀርቶ ከሀገር ውጭ መጓዝ የማይችሉበት ጊዜ ይመጣል።

***ቤን*** አዲስ ጥያቄ አስከተለ። ጥያቄው "እንደ አሜሪካ ፕሬዚዳንቶች መጽሃፍት ቤት መክፈት ይፈልጋሉ?" የሚል ሲሆን መልሳቸው "ሊሆንም ላይሆንም ይቻላል" የሚል ነበረ። ***ቤን*** እንደገና "ብዙ ማጽሃፍት አሎት ማለትን ስለሰማሁ ነው" ሲላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ "አሉኝ" ካሉ በኋላ ሌሎች ያልተጠበቁ ነገሮች ያነሳሉ። ጠቃሚ ስለመሰሉን ያሉትን እንዳለ እናቀርበዋለን።

" እነርሱ (የቀድሞ የአሜርካ ፕሬዚዳንቶች) ብር አላቸው። እኔ ብር የለኝም። የሚያግዝ
ከተገኘ- ቤት ሰርቶ የሚሰጥ ከተገኘ መጽሓፎቹን ለማበርከት ችግር የለኝም። ብዙ
መጽሓፍት እንዳሉኝ የታወቀ ነው። ዋናው ነገር የምፈልገው በሃገሬ ሆኜ የሙሉ ቀን ሥራ
ሳይኖረኝ፣ በአብዛኛው በእረፍት ላይ ሆኜ ለሃገሪቱ - ለድርጅቱ ይጠቅማሉ የምላቸውን
ሥራዎች በትርፍ ጊዜ መስራት ነው። …"

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብር አላቸው ወይስ የላቸውም? እርሳቸውም ባለቤታቸውም የለንም ባይ ናቸው። ሀገሪቱ ልትከፍል የምትችለውን ስጥታቸው በድህነት የሚኖሩ ከሆነ ለምን ሥራውን አይለቁም?፡ በአንድ አጋጣሚ ባለቤቲቱ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጭንቅላት ለእኔና ለልጆቼ ይበቃል ሲሉ መደመጣቸውን እናስታውሳለን። ጠቅላይ ሚንኒስትሩ ራሳቸው በቃለ መጠይቁ ወቅት " የግል ሥራ ብሰራ ውጤቱ አንስተኛ ይሆናል የሚል ግምት የለኝም"

ብለዋል። ቦታውን ላግኝ እንጂ በነጻም ቢሆን አገለግላለሁ የሚል በሞላበት ሃገር ባጭር ጊዜ ሚሊዩነር መሆን የሚችሉ ሰውዮ በድህነት መኖር ይገባቸውል አንልም። ስሞኑን የድህነት ኑሮ አስመርሯቸው የሥራ መልቀቂያ ደብዳቤ ለተወካዩች ምክር ቤት ቢያስገቡ ወዲያውኑ መቀበል ያስፈልጋል። ለአፋቸው አሉት እንጂ ስልጣን ከሁሉም ነገር ስለሚበልጥባቸው ንክች አያደርጓትም።

ሌላው ነገር ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለቤታቸው ገንዘብ የለንም ከሚሉ በስተቀር እንደሌላቸው እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? ዳጎስ ያለው ደመወዛቸው፣ የተለያዩ አበሎቻቸው፣ የቤትና ሌላ የመኖሪያ ወጪዎቻቸው፣ የትምህርታቸው፣ የጥበቃው ወዘተ. በድሃ ታክስ ከፋዩች የሚሸፈን ነው። እኛ እስከምናውቀው ድረስ ገቢያቸውም ሆነ ወጭያቸው የኦዲት ሪፖርት ቀርቦበት አይውቅም። ምን ያህል እንደሆነ የሚያውቅ የለም፣ የሚያውቅ ቢኖርም ምስጢር ስለሆነ አይናገርም። ስለድህነታቸው ገለልተኛ በሆነ አካል የሚቀርብ ማስረጃ እስክናይ ድረስ እርሳቸውም ሆኑ ባለቤታቸው የሚሉትን እንዳለ ወስደን አናስተጋባም። ምንልባትም የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሃብት ድርሻ ያለው ባለ ብዙ ቢሊዩን ጥሬ ዶላርና ንብረት ባለቤት በሆነው EFFORT አካባቢ ይሆናል። EFFORT የሚመራው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለቤት ሲሆን የሃገሪቱን አጠቃለይ ኢኮኖሚ ሰንገው የያዙ ከሰማንያ በላይ ኩባንያዎች በስሩ ይገኛሉ። ድርጅቱ ለይስሙላ የትግራይ ህዝብ ሃብት ተብሎ የተመዘገበ ቢሆንም ድርጅቱን በተለያየ ጊዜ የመሩ ሰዎች አመራሩን ከተረከቡ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ቢጠሯቸው የማይሰሙ ሃብታሞች መሆናቸው ይታያል። ማን ያውቃል? ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለቤታቸው ከዚህ ድርጅት ጋር በተያያዝ ያካበቱት ሃብት ካለ ሥራ ከለቀቁ በኋላ ብቅ ያደርጉ ይሆናል። በትዕግስት መጠበቅ ነው።

በነገራችን ላይ የመንግስት ባለስልጣናት የሃብት ማሳወቂያ የመመዝገቢያ ረቂቅ አዋጅ ለብዙ ዓመታት ሲጓተት ቆይቶ ለተወካዩች ምክር ቤት ከቀርበ ገና ሁለት ሳምንቱ ነው። የሀብት ምዝገባ ወሬ መናፈስ ከጀመረ ብዙ አመታት ያለፉ ሲሆን ባለስልጣናቱ ሃብታቸውን ቦታ ቦታ ለማስያዝ በቂ ጊዜ እንደሰጣቸው ይታወቃል። አንዳንዶቹ ያካበቱት ሃብት ብዛቱ ከህዝቡ ጋር በተቃርኖ ስላቆማቸው ለፖለቲካና ማህበራዊ ድርጅቶች እንዲሁም ለግላሰቦች ሲያስተላልፉ ነበር። ረቂቁ ተመክሮበት ህግ እስኪሆን ድረስ ተጨማሪ ዓመታት ማለፋቸው ስለማይቀር ቀሪውን ቦታ ለማስያዝ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚሰጣቸው ይጠበቃል። ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለቤታቸው በአዋጁ እንደሚሸፈኑና ሃብታቸውን እንደሚያስመዘግቡ፣ የህብታቸውም ዝርዝር ለህዝብ ግልጽ እንደሚደረግ ተስፋ እናደርጋለን። ምናልባት በዚህ የሃብት ማሸሽ ጥድፊያ መሃል አንዱ የሥራ ባልደረባቸው ለመጽሓፍት ቤት የሚሆን ቤት ያበረክትላቸው ይሆናል። ከተሳካ እኛም የመጽሓፍት ቤቱ ተጠቃሚ እንሆናለን።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በእረፍት ላይ ሆነው ለሃገሪቱና ለድርጅቱ ይጠቅማሉ የሚሏቸው ስራዎች መስራት እንድሚፈልጉ ተናግረዋል። ይህ ሥራ ምን ሊሆን እንደሚችል እግዜር ይወቅ። እዚህ ላይ ሰውየው ስለጡረታ እንደማይናገሩ ያስተውሏል። ከፊል ሥራ ሆኖ ደመወዝና አበል የሚከፈልበት፣ የመኖሪያ ቤት ወጭ የሚሸፈንበት፣ የጥበቃ አገልግሎት የሚገኝበት ሥራ ከፈልጉ ያለው ፕሬዚዳንትነት ነው። ሰውየው ከሚሉት መገመት የሚቻለው በዚያ ቦታ ላይ አይናቸውን መጣላቸውን ነው። ቦታው እርሳቸውን የሚተካውን ጠቅላይ ሚኒስትርም ሆነ ካቢኔውን በቅርብ በበቂ ሁኔታ ለመቆጣጠር ያስችላቸዋል። ድርጅት ያሉትን በስም ባይገለጹም ኢህአዴግን ማለታቸው እንደሆነ እንገምታን። ኢህአዴግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከመሩ ከጠቅላይ ሚኒስትርነት ወደ ፕሬዚዳንትነት አፈግፈገው ሃገሪቱን እንደገና በእጃቸው አስገቡ ማለት ነው። ሃያ አምስት ዓመት በጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ ቀሪውን በፕሬዚዳንትነት ከዚያ በኋላ ደግሞ ማን ያውቃል? ባጭሩ ሰውየው ሰላሳም አርባም ዓመት መስራት ከቻሉ ሃገሪቱ አዲስ አስተዳደርም ከእርሳቸው ሌላ መሪም እንዲኖራት አይፈቀድላትም። እርሳቸው በአምሳላቸው የፈጠሯት ልጃቸው ስልሆነች

የሚያሳድጓትም፤ የሚድሯትም ስትሞትም የሚቀብሯት እርሳቸው ብቻ ናቸው። መሪ ይሏል ይሄ ነው።

*ቤን* ይህን አሳዛኝ ሁኔታ እንዴት እንደሚያየው ለማወቅ ዶኩሜንታሪውን ማየት እንናፍቃልን።

*ማጠቃለያ*

*ቤን* ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ያደረገውን ቃለ መጠይቅ መነሻ በማድርግ ባዘጋጀናት በዚች አጭር ጽሁፍ የተነተንነውን በጥሞና ካነበበ በኋላ ያለአንዳች ጥርጣሬ ሰውየው ስለህዝቡና ስለሃገሪቱ የሚናገሩት ከእውነታው የራቀ መሆኑን ይገነዘባል። ይህ ከእውነት የራቀ ንግግር የሚመነጨው ለማሳሳት ከመፈለግ ወይም እውነቱ ከወጣ የሚከተለውን በመፍራት ብቻ ሳይሆን ሰውየው ዓላማዬ ብለው የያዙትን ለማሳካት ከመፈላግም ጭምር እንደሆን ይረዳል። እኛ የምንለው እውነት መሆኑን በቃለ መጠይቁ ወቅት ከተናገሩት በግልጽ መረዳት እንደሚችል ተስፋ እናደርጋልን።

በዚች ጽሁፍ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የደበቋቸው ወይም የዋሿቸውን ጉዳይች በዝርዝር ማሳየት ብቻ ሳይሆን ድብቃውም ውሸቱም ከዓላማቸው ጋር እንዴት እንድተቆራኘ መርመርናል። ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቱን እዚህ መድገም አይከፉም። ይህን ማድረጋችን ትንሽም ቢሆን የ*ቤን*ን ሥራ ያቃልላል ብላን እናስባልን።

በህገ መንግስቱ የተደነገጉ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች እርሳቸው በሚመሩት ድርጅትና መንግስት በገፍ በመጣሳቸው በንዴት ገንፍሎ እንዳይወጣ በሃይል ታፍኖ የተያዘ ህዝብ ዝም ስላለ ተረጋግቶ፤ ሰክኖ መራመድ ጀምሯል ይላሉ። ይህን የሚሉት የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶችን ሁኔታ ለማሻሻል ፍላጎት ስለሌላቸው ነው።

በበደል ብዛት ድርጅታቸውንና መንግስታቸውን በሰላማዊም ሆነ በትጥቅ የሚታገሉ የብሄርና የህብረ ብሄር ድርጅቶች በሞሉበት ሃገር ስላም ሰፍኗል፤ አንድነታችንም ጠንካራና አስተማማኝ ነው ይላሉ። ይህን የሚሉት በትጥቅ የሚታገሉ ወደሰላማዊ ትግል እንዲመጡ ሁኔታውን ማመቻቸት ስለማይፈልጉ ነው።

በሃገራችን ሁኔታ የረሃብና የምግብ እጥረት ልዩነት በሞት መኖር ወይም አለመኖር መለካት እንደሌለበት እያታወቀ ሞት ስላሌለ ረሃብን አሸነፍነው ለማለት ይቃጣቸዋል። ይህን የሚሉት ሀገሪቱ ተረፈ ምርት surplus ከኖራት ማህበራዊ ቀውስ ይከተላል በሚል አጉል ፍራቻ ነው።

85 % የሚሆነውን የሃገሪቱን ህዝብ ያለአንዳች ጥበቃ ለዓለም ዓቀፍ ካፒታል አጋልጠው በግዴላሽነት ሰፋፊ እርሻ ማከራይት አጠናክረን እንገፋበታልን ይላሉ። ይህን የሚሉት ግን ጉዳዩ በበቂ ውይይትና ጥናት ላይ የተመሰረት ጥበቃ እንዲኖረው ማድረግ ስለማይፈልጉ ነው።

በመጪው ምርጫ ህዝቡ ቢያምጽ ክንዳችንን ይቀምሳል በሚል ይስፈራራሉ። ይህን የሚሉት በምርጫም ወቅት ቢሆን ህዝቡ ህገመንግስታዊ መብቶቹን እንዲጠቀም ስለማይፈልጉ ነው።

**በዚህ ሁኔታ የሃገሪቱን አንድነት መጠበቅም ሆነ ልማትዋን ማፋጠን አይቻልም። በሁሉም መስክ መሰረታዊ መሻሻል ካልታየ መጪው ጊዜ በማያጠራጥር ሁኔታ ለሁላችንም አስቸጋሪ ይሆናል።**
**እንደሃገርና እንደህዝብ መኖራችንም ያበቃለታል።**

+++++++++++++++++ ++++++++++++++++